ኢፕድ

# አዲስ ዘመን


ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 276 ሰኔ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የኦሮሚያ ክልል ከ413 ሚሊዮን በላይ

## የሻይ ቅጠል ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት አደረገ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል በመጪው ክረምት ወቅት ከ413 ሚሊዮን በላይ የሻይ ቅጠል ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት ማድረጉን አስታወቀ። ሀገሪቱ በዘርፉ ከምታገኘው ገቢ 70 በመቶ ያህሉ የሚሸፈነው በክልሉ እንደሆነ ተጠቁሟል።

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የቡናና ሻይ ዘርፍ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሐመድሳኒ አሚን በክልሉ ያለውን የሻይ ቅጠል ልማት ያለበትን ሁኔታ አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ማብራሪያ፤ ክልሉ የሻይ ቅጠል ልማትን ጨምሮ በግብርና ውጤቶች ካለው አቅም አንጻር የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን በስፋት እያከናወነ

የኦሮሚያ ክልል ... ወደ ገጽ 14 ዞሯል






# በኢትዮጵያ

## ገጠራማ አካባቢዎች 2 ሺህ የጤና ማዕከላት ሊገነቡ ነው

**- አራት ሚሊዮን ዜጎችን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ያደርጋል**

ገጽ 14



# መንግሥት የፕሪቶሪያ

## የሰላም ስምምነትን ተግባራዊ በማድረግ ብዙ ርቀት ተጉዟል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በትግራይ ክልል የሰብዓዊ አቅርቦት ተደራሽ በማድረግ፣ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ በመገንባትና በጀት በመመደብ የሰላም ስምምነትን

መንግሥት የፕሪቶሪያ ... ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ተረጂዎችን በተመለከተ የሚቀርቡ የተዛቡ መረጃዎች

## ትክክለኛነታቸው ሊጣራ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ተሰጠ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ ፡- የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ድጋፍ የሚሹ ወገኖችን በተመለከተ ለሚቀርቡ የተዛቡ መረጃዎች ትክክለኛነት ሊጣራ እንደሚገባ ተገለጸ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ጉዳይና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) የኮሚሽኑን ሥራዎች የመስክ ምልከታ ትናንት በተደረገበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ተቋሙ የተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል እየሠራ ነው። ችግር ሲደርስም ለተጎጂዎች ተገቢውን ድጋፍ የማድረግና መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን በጠንካራ አቋም እያከናወነ ይገኛል።

ይህም ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች ለፖለቲካ ትርፍና ሌሎች ጥቅሞች ሲባል የተረጂዎችን ቁጥር በተጋነነ መልኩ መጨመር በስፋት ይስተዋላል ያሉት ዲማ (ዶ/ር)፤ ይህ አካሄድ በርካታ ችግሮችን የሚያስከትል ሲሆን የተረጂነት መንፈስንም የሚያስፋፋ ይሆናል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ተረጂዎችን በተመለከተ የሚቀርቡ የተዛቡ አሃዞችን ትክክለኛነታቸውን በማጣራት ድጋፍ የማድረግና



እውነታውንም ለሕዝብ የማድረስ ሥራዎችን አጠናክሮ ሊሠራ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አምባሳደር ዶክተር ሺፈራው ተክለማርያም በበኩላቸው፤ የተረጂዎችን አሃዝ አጋኖ የማቅረብ ችግር በስፋት እንደሚስተዋል በመግለጽ፤ የተጠያቂነት አሠራር ለማስፈን እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የተረጂዎችን ቁጥር

ተረጂዎችን በተመለከተ ... ወደ ገጽ 14 ዞሯል




# በወላይታ ዞን በዘንድሮ ዓመት 162 ሺህ ኩንታል እሸት ቡና ተሰብስቧል

## - ስድስት ሺህ ኩንታል ቡና ለውጭ ገበያ ቀርቧል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ዞን ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም ጀምሮ 162 ሺህ ኩንታል እሸት ቡና መሰብሰቡን የዞኑ ቡናና ቅመማ ቅመም ጽህፈት ቤት ገለጸ። ከዞኑ ስድስት ሺህ ኩንታል የቡና ምርት ለውጭ ገበያ መቅረቡን ተጠቁሟል።

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ክፍሌ ካውሌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮ ዓመት የምርት ዘመን ከዞኑ 162 ሺህ ኩንታል እሸት ቡና ተሰብስቧል።

የዞኑን የቡና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተለያዩ የግብርና ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመው፤ አምራች አርሶ አደሮች ጥራት ያለው ቡና እንዲያዘጋጁ የሚረዱ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች መከናወናቸውን አንስተዋል።

ከቡና ወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ ከዞኑ ስድስት ሺህ ኩንታል ምርት ለውጭ ገበያ መላክ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዓለም የቡና ገበያ መውረድ ጋር ተያይዞ የዞኑ የቡና ገበያም የመቀነስ አዝማሚያ እንዳለው አመላክተው፤ በቀጣይ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ድረስ ወደተለያዩ ሀገራት የሚላክ የቡና ምርት መኖሩን አመላክተዋል።

በዞኑ ቡና በሁለት ዓይነት መንገድ ለገበያ እንደሚቀርብ የተናገሩት ኃላፊው፤ የመጀመሪያው ቡና ታጥቦ እንዲቀርብ ይደረጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ቡናን በልዩነት ደርቆ ለገበያ እንዲቀርብ የሚደረግበት አሠራር መኖሩን ገልጸዋል።

አቶ ክፍሌ እንደተናገሩት፤ በዞኑ 36 አባላትን ያቀፈ የቡና አቅራቢ ማህበር አለ። የማህበራትን ቁጥር ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

በሌላ በኩል ከዚህ በፊት ነጋዴዎች በተበታተነ መልኩ በራሳቸው ቡናን ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን፤ አሠራሩን በመቀየር በማህበር እንዲደራጁ ለማድረግ ትኩረት መሰጠቱን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በዞኑ በሚገኘው የቡና ማህበር አማካኝነት ምርቱን ለውጭ ገበያ እንደሚቀርብ አስታውሰው፤ አሁን ላይ የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ነጋዴዎችን በመለየት በቀጥታ ወደውጭ ሀገራት እንዲልኩ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ቡና በማጠብና በመፈልፈል የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን የማጠናከር እንዲሁም ከዚህ በፊት ቡናን በማምረት ውጤታማ ከሆኑ አካባቢዎች የልምድ ልውውጥ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ከመስከረም 2017 ዓ.ም ወር ጀምሮ ቡና በስፋት ወደገበያ የሚገባ እንደመሆኑ ነጋዴዎች ቀደም ብለው



ዝግጅት እንዲያደርጉና ከብድር አቅርቦት ጋር ተያይዞ ባንኮች ትብብር እንዲያደርጉ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ጥሪ አቅርበዋል።

# በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራትና ማሳን ለማዘጋጀት አዎንታዊ ሚና እንደሚኖራው የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ፤ በሚቀጥሉት ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ አስታውቋል።

ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ምዕራብ ማዕከላዊና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ አዊ ዞን ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደ ሚኖራቸው ተመላክቷል።

ከትግራይ ክልል ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ መተከል እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ ዳውሮ፣ ከፋ ሸካ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሃዲያ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኙዋክ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ንዌር ዞኖች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል ተብሏል።

በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ባሌና ምሥራቅ ባሌ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረር፣ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ ከትግራይ ክልል የደቡብ ምሥራቅና የመካከለኛው ትግራይ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ አማሮ፣ አሌ፣ ቡርጂ ደራሼ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ሀሪ ጋቢ እና ሀውሲ ዞኖች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቁሟል።

በሚቀጥሉት ዘጠኝ ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት አስቀድመው የሚዘሩ የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራትና ማሳን ለማዘጋጀት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ዘግይተው ለተዘሩ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ አትክልቶች፣ ለጓሮ አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው በመግለጫው ተመላክቷል።

በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት፣ ለቋሚ ተክሎች፣ በአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ ለተተከሉ እና ለሚተከሉ የዛፍ ችግኞች እድገት የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

በሌላ በኩል በሚቀጥሉት ቀናት በዓባይ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ እና ተከዜ እንዲሁም በጥቂት የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ። ይህ የእርጥበት ሁኔታም በተፋሰሶች ላይ የሚኖረውን የገፀ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን ያሻሽላል፤ ለመስኖም ሆነ ለኃይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ የግድቦችን የውሃ መጠን ያሻሽላል ተብሏል፡



# የግብርና ባለሙያዎች ማህበራት ጥምረት ለግብርናው መዘመን ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የግብርና ባለሙያዎች ማህበራት ጥምረት ለግብርናው መዘመን ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተጠቆመ። የኢትዮጵያ የግብርና ባለሙያዎች ማህበራት ጥምረት ትናንት ተመስርቷል።

የኢትዮጵያ የግብርና ባለሙያዎች ማህበራት ጥምረት የምስረታ መርሀ ግብር ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ማንደፍሮ ንጉሴ(ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ የግብርና ባለሙያዎች ተቀናጅቶ መሥራት ለግብርናው ዘርፍ እድገት ወሳኝ ነው። በተለይ አዳዲስ አሠራሮችና ምርምሮችን ወደ ተግባር በመቀየር ግብርናውን ማዘመን ያስችላል።

የባለሙያዎች በጋራ ተቀናጅቶ መሥራት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዓለም የትብብር በመሆኗ ብቻውን ተነጥሎ የሚወጣ ግለሰብም ሆነ ተቋም ስኬታማ እንደማይሆን ተናግረዋል።

በመተባበርና በመተጋገዝ የጋራ ራዕይ በመያዝ ኢትዮጵያ መድረስ ያለባት ደረጃ ላይ እንድትደርስ በምንችለው አቅም መሥራት አለብን ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዘርፉ ያሉትን ምሁራን በአግባቡ በመጠቀም ለውጥ ማምጣት አለብን ብለዋል።

የግብርና ባለሙያዎች ማህበራቱ ጥምረት መመስረት ለኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ ማደግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልጸው፤ ጥምረቱ እስከሚጠናከር የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እገዛ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

በምስረታ መርሀ ግብሩ ላይ የምስረታ ጽሁፍ ያቀረቡት ሀብቱ አሰፋ(ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከዚህ በፊት የነበረው የግብርና ባለሙያዎች ማህበር የፖሊሲ ቀረጻ ላይ እንዲሁም አዳዲስ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ የማድረግ ዓላማ ይዞ የተመሠረተ ቢሆንም ማሳካት ሳይችል ቆይቷል።

አዲስ የተመሠረተው ጥምረት የነበረውን ክፍተት በመሙላት በሀገሪቷ በሚከናወኑ የፖሊሲ ቀረጻ ላይ እንዲሁም የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ለመንግሥት አካል እያቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል ብለዋል።

በኢትዮጵያ እስከ 15 የሚደርሱ የግብርና ባለሙያዎች ማህበራት መኖራቸውን ተናግረው፤ 10 የሚሆኑት የማህበራቱ ጥምረቱን በጋራ መመስረታቸውን ተናግረዋል።

የተመሠረተው የግብርና ማህበራት ጥምረት ግብርና ነክ ጥናቶች ማድረግ ፣የፖሊሲ ጥናት ትንተና ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ ጥናቶች ቢያስፈልጉ ትልቅ የባለሙያዎች ስብስብ የያዘና የጥምረቱ መመስረት ባለሙያዎች በተሻለ መልኩ ተቀናጅተው ለመሥራት እንደሚያግዛቸው ሀብቱ(ዶ/ር) ገልጸዋል።

ጥምረቱ አዳዲስ ሃሳቦች በማመንጨት ትልቅ ሥራ እንደሚያከናውን ጠቁመው፤ ውጤታማነቱን በመከታተልም ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

ጥምረቱ አስር አባላት ያሉት የየማህበራቱ ፕሬዚዳንቶችን የያዘ የአስተዳደር ቦርድ የተሾመለት ሲሆን፤ ፕሬዚዳንት፣ ጸሐፊ፣ ሂሳብ ሹም እና ኦዲትም ከመካከላቸው ተመርጧል። ጥምረቱ ከአንድ ወር በኋላ ወደ ትግበራ በመግባት የግብርናው ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን እንደሚሠራም በመድረኩ ተገልጿል።

የምስረታው መድረክ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በጋራ ያዘጋጁት መሆኑ ታውቋል።

# የቀሪና የድጋሚ ምርጫ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ከአንድ ሚሊዮን 46 ሺህ በላይ መራጮች ተመዝግበዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የስድስተኛው ዙር ቀሪና ድጋሚ ጠቅላላ ምርጫ በሚካሄድባቸው ክልሎች ከአንድ ሚሊዮን 46 ሺህ በላይ መራጮች መመዝገባቸውን የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ገለጸ። ምርጫው ወደ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም መሸጋገሩንም ገልጿል።

የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ ሜላተወርቅ ኃይሉ ለጋዜጠኞች ከትናንት በስቲያ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ የስድስተኛው ዙር ሀገራዊ ምርጫ ቀሪ ምርጫ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋር እንዲሁም ድጋሚ ምርጫ በጅግጅጋ እና መስቃን ማረቆ ምርጫ ክልሎች ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. ይካሄዳል። ለዚህም ከአንድ ሚሊዮን 46 ሺህ በላይ መራጮች ተመዝግበዋል። ከዚህ ውስጥ 564 ሺህ በአፋር፣ 265 ሺህ በቤንኒሻንጉል ጉሙዝ እና ቀሪዎቹ በሶማሌና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ምርጫውን ለማካሄድ 1 ሺህ 285 ምርጫ ጣቢያዎችና 6 ሺህ 380 ምርጫ አስፈጻሚዎች መዘጋጀታቸውንም ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንን ጨምሮ 7 ድርጅቶች ታዛቢዎችን ለማሰማራት ጥያቄ አቅርበዋል ብለዋል። በአራቱ ክልሎች ለሚወዳደሩ 11 የፖለቲካ ፓርቲዎች በድምሩ 21 ሚሊዮን ብር ድጋፍ መደረጉንም ተናግረዋል።

በምርጫው 11 የፖለቲካ ፓርቲዎችና 380 የፓርቲና የግል ተወዳዳሪዎች እንደሚወዳደሩ የገለጹ ሲሆን፤ ድምጽ አሰጣጥና የመራጮች ምዝገባ በአንድ ቀን ከሚካሄድባቸው መስቃን ማረቆ እና ጅግጅጋ የምርጫ ክልሎች ላይ የተወሰደውን ግምት ጨምሮ አንድ ሚሊዮን 46 ሺህ መራጮች በምርጫው ተመዝግበዋል ብለዋል።

በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ መስቃንና ማረቆ የምርጫ ክልሎች የመራጮች ምዝገባና ድምጽ አሰጣጥ በአንድ ቀን ይከናወናል። የዚህም ምክንያት በእነዚህ አካባቢዎች የነበረው የመራጮች መረጃ የተሟላ ሆኖ ቦርዱ አለማግኘቱን ገልጸዋል።



**ሜላተወርቅ ኃይሉ፤**

የስድስተኛው ዙር ቀሪና ድጋሚ ጠቅላላ ምርጫ በሚካሄድባቸው ክልሎች የድምፅ መስጫ ወረቀት ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መጓጓዝ መጀመሩን የገለጹት የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ፤ ሜላተወርቅ ቦርዱ ተወዳዳሪ እጩዎችን አጣርቶ በመለየት የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት በክልሎች ከሚወዳደሩ 11 የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ምክክር ማድረጉንም ተናግረዋል።

ቦርዱ የመራጮችና እጩዎች ምዝገባን እየተከታተለ መሆኑን ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የራሱን ቡድን በማዋቀርና ከተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመመካከር በአራቱም ክልሎች ምርጫ ማከናወን የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩን አረጋግጠናል ብለዋል።

ይህ የድጋሚ ምርጫ የሚካሄደው ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ከተካሄደ ከሦስት ዓመታት በኋላ ሲሆን፤ ቀደም ብሎ ምርጫው እንዲከናወን የታቀደበት ቀን ማለትም ሰኔ ዘጠኝ ቀን 2016 ዓ.ም. ከሃይማኖታዊ በዓል ጋር ስለተገጣጠመ የምርጫውን ቀን ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምርጫው ወደ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. መሸጋገሩን ቦርዱ ገልጿል።

በተመሳሳይ ቦርዱ በትግራይ ክልል የዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል። በክልሉ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችል ፈቃጅ ሁኔታ ሲፈጠር ምርጫ የሚካሄድ ይሆናል ያሉት የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ ሜላተወርቅ፤ ለዚህም ቦርዱ በምርጫ ክልሉ ያለውን ቢሮ አጠናክሯል። በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል አደራጅቷል ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ቦርዱ የምርጫ ትምህርት መስጫ ህትመቶችን በትግርኛ ቋንቋ አስተርጉሞ እያዘጋጀ ይገኛል ያሉት የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ ሜላተወርቅ፤ ቦርዱ በክልሉ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ምርጫ ለማድረግ የዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

# አዋጆቹ ተቃዋሚዎችን ለማፈን እንዳይውሉ ተገቢ ድንጋጌዎች እንዲካተቱባቸው የምክር ቤት አባል አሳሰቡ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይንም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እንዲሁም የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጆች ገዢው ፓርቲ ተቃዋሚዎችን ለማሳደድ እና ለማፈን እንዳይውሉ ለማድረግ ተገቢ ድንጋጌዎች እንዲካተቱባቸው አንድ የምክር ቤት አባል አሳሰቡ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትናንት በስቲያ ባካሄደው 31ኛ መደበኛ ስብሰባው የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅና በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ረቂቅ አዋጆችን ተመልክቶ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

የምክር ቤት አባሉ ደሳለኝ ጫኔ (ዶ/ር) ተጠያቂነትን ለማስፈንና ሕገወጥ አሠራርን ለመከላከል ከሆነ በበጎነት የሚታይና እንደዚህ አይነት የጸረ ሽብር ሕጎች አስፈላጊም መሆናቸውን ተናግረዋል። ነገር ግን ከዚህ ቀደም ጸድቀው ሲተገበሩ የገዢው ፓርቲ ወይንም መንግሥት ተቃዋሚዎችን ለማጥቃት ሲውል እንደነበር በተለያዩ ሁኔታዎች ሲገለጽ እንደነበር አስታውሰዋል።

የሚመራላቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ሲመለከቷቸው አዋጆቹ በትክክል የወንጀል ፍሬ የሆኑትን ብቻ ለይተው ለመከታተል፤ በሌላ በኩልም የፖለቲካ መሳሪያ ሆነው ተፎካካሪ ፖለቲከኞችን ለማሳደድ እንዳይውሉ ተገቢ ድንጋጌዎችን እንዲካተቱባቸው ማድረግ ይገባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ተቋማትና የመብት ተከራካሪ ድርጅቶች እንደዚህ አይነት ሕጎችን በስጋት ይመለከቷቸዋል። ከዚህ ቀደምም ተቃዋሚዎችና መንግሥትን የሚተቹ ሰዎች የእነዚህ አይነት ሕጎች ሰለባ ሆነው ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል ነው ያሉት።

ሌሎች የምክር ቤት አባላት በሰጡት አስተያየትም ሕጉ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚነካ መሆኑን አንስተዋል። በሕገወጥ መንገድ የሚወጣውን ገንዘብ ለመከላከል እና ለማዳን እንደሚያደርግ፣ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል እንደሚጠቅም ተናግረዋል።

ሕጉ የሚመራለት ኮሚቴ የዓለም የገንዘብ ድርጅት ያወጣቸውን እና ሀገራት የግድ እንዲቀበሏቸው የተቀመጡ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን ኢትዮጵያ ካወጣቻቸውና ተቀብላ ካጸደቀቻቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ለምክር ቤቱ የተደራጀ ሰነድ እንዲያቀርብም አሳስበዋል።

በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን ረቂቅ አዋጅ ለምክር ቤት አባላት ያቀረቡት በምክር ቤቱ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ መሰረት ኃይሌ፤ ወንጀሉ የደህንነት ስጋት ከመሆኑ በተጨማሪም የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጽ፣ ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደርገዋል ብለዋል።

ቀድሞ የነበረው አዋጅ ቁጥር 780/2013 ግልጽነት የጎደለውና በተግባር ችግር የፈጠረ በመሆኑ ከሌሎች ሕጎች ጋር የማይጣጣም፣ ለወቅታዊ ችግሮች በቂ ምላሽ የማይሰጥ ሆኖ በመገኘቱ መቀየር አስፈላጊ መሆኑንም ነው ያነሱት።

በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ የጥረቱ አካል በመሆኗ እንዲሁም ሕጉን በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ አዋጁን ማውጣት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የንብረት ማስመለስ አዋጅን አስመልክተው ባቀረቡት ማብራሪያ እንዳመለከቱትም፤ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የግብር ሥርዓት፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ዝውውር ሥርዓት እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

ዓላማው የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ ወይም ለመውረስ እንዲሁም ለማስተዳደር የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል።

የሕግ ማዕቀፉም በመንግሥትና በሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ችግሩን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት ማስፈለጉንም ወይዘሮ መሠረት ተናግረዋል። አዋጆቹ በሁለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ ተመርተዋል።

# በክልሉ በአረንጓዴ አሻራ 18 ነጥብ 5 ሚሊዮን የፍራፍሬ ችግኞች ይተከላሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- አማራ ክልል በ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 18 ነጥብ 5 ሚሊዮን የፍራፍሬ ችግኞችን ለመትከል ማቀዱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ እስመለዓለም ምህረቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ለ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የተለያዩ ዝግጅቶችን እያደረገ ይገኛል።

አማራ ክልል በ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አንድ ነጥብ 59 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል አቅዶ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ እስካሁን አንድ ነጥብ 34 ቢሊዮን ችግኞችን ለተከላ ዝግጁ በማድረግ የእቅዱን 76 በመቶ ማሳካት መቻሉን አስታውቀዋል።

የሚተከሉት ችግኞች ፍራፍሬ፣ ለደን ሽፋን፣ ለምግብነትና የአፈር ለምነትን የሚጨምሩ እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ የሚያገለግሉ የዛፍ ዝርያዎች መሆናቸውን አስረድተዋል።

አጠቃላይ ከሚተከሉት አንድ ነጥብ 59 ቢሊዮን ችግኞች መካከል 18 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚሆኑት የፍራፍሬ ችግኞች መሆናቸውን ገልጸው፤ አቡካዶ፣ ማንጎና ሌሎች የፍራፍሬ አይነቶች በዋናነት የሚተከሉ መሆናቸውን አመላክተዋል።

እንደ እስመለዓለም ገለጻ፣ ለተከላ ዝግጁ ከተደረጉት ችግኞች መካከል ከ299 ሚሊዮን በላይ በፕላስቲክ የተዘጋጁ ናቸው። 201 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች ሲሆኑ፤ በቆላማ ቀበሌዎችና ወረዳዎች አካባቢ እስከ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ቆጠራ የሚደረግ በመሆኑ ቁጥሩ ሊጨምር ይችላል ብለዋል።

ችግኞች ለተከላ የማለማመድ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ሥራቸውን የመቁረጥ፣ ውሃ የማጠጣትና ሌሎች ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ከችግኝ ዝግጅት ጎን ለጎንም የመትከያ ቦታዎችን



የመለየት፣ ጉድጓድ የመቆፈር እና ችግኞችን የማጓጓዝ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ለችግኝ ተከላው ከ201 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የመለየት ሥራ መሠራቱን አመልክተው፤ እስካሁን በተሠራው ሥራ ከ400 ሚሊዮን በላይ ጉድጓዶችን ማዘጋጀት ተችሏል። የጉድጓድ ዝግጅቱን እስከሚቀጥለው ሳምንት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የተከላ ማስፈጸሚያ ሰነድ በማዘጋጀት ለሁሉም ዞኖች እንዲደርስ ተደርጓል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የዝናብ ስርጭቱን መነሻ በማድረግ እንደ ክልል ሰኔ 6 ቀን 2016 ዓ.ም የችግኝ ተከላውን ለመጀመር እቅድ መያዙን አመላክተዋል።

የግብርና ባለሙያዎች ለተከላ የደረሰውን ችግኝ ለተከላ የማለማመድ፣ ጊዜያዊ ችግኝ ጣቢያዎች በማቋቋም ችግኞችን የማጓጓዝ እና የሚተከሉበትን የጉድጓድ ዝግጅት የማጠናቀቅ ሥራ ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አርሶ አደሮችም የሚተክሉበትን ቦታ አዘጋጅተው የመጠበቅ፣ የሚተከሉትን የችግኝ ዓይነት በወቅቱ የመጠየቅ እና ለሚተክሉት ችግኝ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ጨምረው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ውጤታማ ባለብዙ ወገን ግንኙነትን ለማስፈን ቁርጠኛ ናት

ኢትዮጵያ ሁሉንም ባማከለ መልኩ ከሀገራት ጋር ግንኙነት ታደርጋለች፡፡ ለሕዝብና ለሀገር እስከጠቀመ ድረስ በገለልተኝነት መርህ ከአራቱም ማዕዘናት ጋር አብራ ትሠራለች፤ ወዳጅነት ትመሰርታለች፡፡ በዚህም ከምሥራቁም ሆነ ከምዕራቡ ሀገራት ጋር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመመስረት በሰላምና ልማት ዙሪያ አብራ በመሥራት ላይ ትገኛለች፡፡ከቅርብ ጊዜያት ወዲህም ብሪክስን በመቀላቀል ሰላምን ፣ ዕድገትን፣ ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በመጣር ላይ ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ ብሪክስንም ስትቀላቀል እነዚህን ዓላማዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተለይም በአሁኑ ነባራዊ የዓለም ሁኔታ ወቅታዊ እና አንገብጋቢ የሆኑ ድንበር ዘለል ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችም በየትኛውም ተቋም ለብቻ ሊፈቱ ስለማይችሉ እውነተኛ ዓለም አቀፋዊ አጋርነት የግድ ይላል፡፡ ብሪክስ ደግሞ የኢትዮጵያም ሆነ የሌሎች ሀገራት ምርጫ እየሆነ መጥቷል፡፡

የብሪክስ አባል ሀገራት 40 በመቶውን የዓለም ሕዝብ ይይዛሉ። ቀደም ብለው ብሪክስን የመሰረቱት ብራዚል፣ ሩስያ፣ ቻይና ህንድና ደቡብ አፍሪካ በጋራ ያላቸው ምጣኔ ሀብታዊ አቅም ደግሞ የዓለምን 26 በመቶ የሚሸፍን ነው። ይህ ምጣኔ ሀብታቸውም በየጊዜው እየጨመረ በዓለም የንግድ ልውውጥ ላይ ተጽዕኗቸው እያደገ ነው።

ይህን ግዙፍ ጎራ ለመቀላቀል በርካታ ሀገራት ጥያቄ እያቀረቡ የሚገኙ ቢሆንም የተሳካላቸው ግን ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥቂት ሀገራት መካከል ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ኢራን፣ ሳውዲ አረቢያ ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች፣ ግብፅ እና አርጀንቲናንም ባለፈው ነሐሴ ደቡብ አፍሪካ ላይ በተካሄደው ስብሰባ አባልነታቸው ተቀባይነት አግኝቷል።የእነዚህ ሀገራት በቡድኑ መካተት ከወዲሁ የብሪክስን አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) ከዓለም አቀፉ የሀገር ውስጥ ምርት ውስጥ 36 በመቶ አድርሶታል። ከዓለም አጠቃላይ ሕዝብም 47 በመቶውን እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

ኢትዮጵያ የብሪክስ ቡድንን ለመቀላቀል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱን ተከትሎ በአሁኑ ወቅት ከመስራቾቹ ቀጥሎ በሁለተኛ እረድፍ ላይ የቡድኑ ባለድርሻ ሆናለች፡፡ይህም ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ዲፕሎማሲና የምጣኔ ሀብታዊ ድል ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የዚህ ብሎክ አባል መሆኗ በርካታ ጠቀሜታዎች የሚያስገኙላት ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ቀዳሚው የኢኮኖሚ ትብብር ነው።በዚህ የኢኮኖሚ ትብብር ኢንቨስትመንትን እና ንግድን ከማበረታት ጋር ተያይዞ በተለይ በአባል ሀገራት ዙሪያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ሪሶርስ እና ገበያ አለ ተብሎ ስለሚታሰብ ብሪክስ አባል ሀገራት እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ እና የኢንቨስትመንት ሥራ ኢትዮጵያ ትልቅ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ትሆናለች ተብሎ ይታሰባል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ፈጣን ዕድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙ ሀገራት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ እንደመሆኑ መጠን የብሪክስ አባል ሀገር መሆኗ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ ድጋፍ ይሆናታል፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ እየገነባቻቸው ለሚገኙ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ብድርና እና እርዳታ ከማግኘት አንጻር ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ የብሪክስ ማኅበር የፈጠረው ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ (New Development Bank) በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ ለመሠረተ ልማት እና ለዘላቂ ልማት ፕሮጀክቶች ሀብት የማሰባሰብ ዓላማ ያለው ከመሆኑ አንጻር ኢትዮጵያም የዚሁ ዕድል ተጠቃሚ የምትሆንበት ዕድል የሰፋ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የኃይል ማመንጫ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን፣ ሰፋፊ የግብርና ሥራዎችን፣ የመንገድ መሠረተ ልማቶችንና ኢንዱስትሪዎችን የምትገነባ ሀገር በመሆኗ ሰፊ መዋዕለ ንዋይ ያስፈልጋታል፡፡ ለዚህ ግብዓት የሚሆን ድጋፍ እና ብድር ከእነዚህ ሀገራት ይገኛል ተብሎ ይታሰባል። እንደ ቻይና እና ሩስያ ከመሳሰሉ ሀገራትም የብድር ተቀናሽና ስረዛ ለማግኘትም ዕድል ይሰጣል፡፡

ከምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው ጎን ለጎንም የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲዊ ተሰሚነት የሚጨምር ነው፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ የምትከተለውን ከሁሉም ወገን ጋር አብሮ የመሥራት አካሄድ ለመተግበርና ከምዕራቡም ከምሥራቁም ዓለም ጋር በወዳጅነት ለመዝለቅ የምትከተለውን ሚዛን የጠበቀ ግንኙነት ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችላት ነው፡፡

በሩሲያ ኒዥኒ ኖቭጎሮድ እየተካሄደ በሚገኘው የብሪክስ የውጭ ጉዳይ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ተወክላ በመሳተፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ስብሰባውም ኢትዮጵያ ከብሪክስ አባል ሀገራት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የኢኮኖሚ ትብብሯን ለማጠናከር የሚረዳት ነው፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በተለይ ካለፉት አምስት ዓመታት ጀምሮ እያስመዘገበች ያለችውን የዘላቂ ልማት ግቦችንና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎችን ወደ መሬት አውርዶ የሕዝቡን ኑሮ ለመለወጥ ብሪክስን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ አጋሮች የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ በሕዝብ ቁጥር ብዛቷና እያስመዘገበችው ባለው ፈጣን እድገት የብሪክስ አቅም እንደምትሆን እምነት የተጣለባት ከመሆኑም ባሻገር ብሪክስ ኢትዮጵያ ለተያያዘችው የልማት ሥራዎችም አዳዲስ ዕድሎችን የመፍጠር አቅም ያለው ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሁሉም ስለ ሀገር ሰላም!

**በምስጋና**

ዓለምን ወደ አንድ መንደር ለማምጣት ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ሀገራት ዓላማቸውን እውን ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ የመመልከቱ ጉዳይ አዲስ አይደለም፡፡ እጅን በአፍ የሚያስጭኑ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በአንዱ ተገርመን ሳናበቃ እንዳሻቸው ይፈራረቃሉ፡፡ በአህጉራችን አፍሪካ ግን ወደ ዓለም አስተሳሰብ ለመጠጋት ያሉ ጥረቶች የሚበረታቱ ናቸው ብሎ ለመናገር ያዳግታል፡፡ ጅምሮች እንኳን ቢኖሩ ቀጣይነታቸው አጠያያቂ ሆኗል፡፡

በእርግጥ ለችግሩ ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻል ይሆናል፡፡ የስልጣኔ እና የኋላቀርነቱ ችግር ተደራርቦ ካመጣው ባልተናነሰ የምዕራባዊያንም ሆነ የሌሎች ሀገራት ቀጥተኛም ሆነ የእጅ አዙር ጫናዎች ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› እንዲሉ፣ በአንዱ ችግር አንዱ እንዲደረብ ሰፊ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በኢኮኖሚ ብዙ እድገት እንዳይመዘገብ ጎታች ምክንያት ሆኗል፡፡ በግብርናውም ይሁን በሌሎችም ምጣኔ ሀብታዊ ዘርፎች ራስን ከመቻል ይልቅ ተመጽዋችነትን ምርጫ እንዲሆን አስገድዷል።

በአህጉሪቱ ከስልጣኔ ይልቅ ኋላቀርነት ገዝፎ ይታያል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ ከመማር ይልቅ ትምህርት ቤቶችን ማውደም ቀሏል፡፡ ውይይትና ንግግርን ከማስቀደም ይልቅ የእርስ በእርስ ጦርነት እንደአማራጭ ይወሰዳል። የአህጉሪቷ ሕዝብ እንደዚህ ያሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ቆም ብሎ ‹‹ ግን ለምን?›› የሚለውን ጥያቄ የማንሳት ሞራል እንዳይኖረው በተለያዩ ትርክቶች ተተብትቧልና እንዴት ይህን ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል?

በሀገራችንም ቢሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች በሰላም ወጥቶ የመግባቱ ነገር ፈተና ሲገጥመው ታዝበናል፡፡ ለአብነት የትምህርቱን ዘርፍ አንስተን ብናይ ብዙ ፈተናዎችን እንደገጠመው መጥቀስ ይቻላል። ከሁለት ዓመታት በፊት እንኳን በተፈጠረው ጦርነት ሳቢያ ምን ያህል ትምህርት ቤቶች እንደወደሙ እና በርካታ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዲርቁ እንዳስገደዳቸው የሚዘነጋ ክስተት አይደለም፡፡

ሁሉም ሀገራት ኢትዮጵያን ይወዳሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን ከማድረግ ባሻገር የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈጸም አበክረው የመሥራታቸው ነገር አዲስ አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ የገዛ ልጆቿን በገንዘብ እና በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በማማለል እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ይህ አይነቱ ድርጊት ዛሬ የተፈጠረ ወይም አዲስ ነገር አይደለም፡፡ እንደውም የብዙ ዓመታት ልምድ የተካበተበት ጭምር መሆኑን የታሪክ ምስክር ነው፡፡ እዚህ ጋር ያለው ልዩነት የሀገራቱ መለያየት ብቻ ሲሆን፤ በዓላማ ግን አምሳያ ናቸው፡፡

የሰላም ዋጋው ብዙ ብቻ ሳይሆን በምንም ሊተመን የሚችል እንዳልሆነ ነጋሪ አያሻም፡፡ እንደ ሀገር በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ፍጻሜያቸው የሚያምረው የሰላም አየር ምድሪቱን ሲያውድ እና ሲሞላ ብቻ ነው፡፡ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራቱ ነገር የሚሰምረው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው፡፡ የዛሬ ፍሬዎች አድገው እና አብበው ሀገራቸውን የሚጠቅሙት ሰላም ኖሮ ወደ ትምህርት ቤታቸው ሲያቀኑ ብቻ ነው፡፡

ሁሉም ሃይማኖቶች ሰላምን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን እና እርቅን በመስበክ፤ ተከታዮቻቸው እነዚህን መልካም ተግባራት በተግባር እንዲያውሉ እና ከሁሉም ጋር በፍቅር እንዲኖሩ የማድረግ አቅም እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ በዘር እና በሃይማኖት አክራሪነት ተጠልፈው ወይም ተከልለው፤ ኢትዮጵያ እያስተናገደች ካለው ፈተና በተጨማሪ ሌላ ፈተና ሲፈጥሩባት ይስተዋላል፡፡

የተለያዩ ሃይማኖቶች አምልኳቸውን ለመፈጸም፣ አማኞቻቸውን ለመገሰጽ፣ ለማስተማርም ሆነ ስለ ሀገር ሰላም ለመጸለይ እንኳን ሰላም አስፈላጊ መሆኑን መናገር ለቀባሪው እንደማርዳት ያለ ቢሆንም፤ ሰላም ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ማስገንዘብ ያሻል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት በነበረው የሰሜኑ ጦርነት፤ የጦርነትን አክሳሪነት ለመረዳት የታሪክ መዛግብት ሳናገላብጥ በዘመኑ የታሪክ ተካፋይ በመሆናችን ብቻ ብዙ ትምህርት እንድናገኝ ዕድል ሰጥቶናል፡፡ በዚህም የጦርነት ትርፉ ሞት፣አካል ጎዳተኝነት፣ ርሃብ፣ የኢኮኖሚ ድቀት፣ መፈናቀል፣ ከትምህርት መገለል፣የተገነቡ መሠረተ ልማቶች ውድመት፣ ሰብአዊ እና የጤና እርዳታዎችን ለማግኘት መቸገር እና የመሳሰሉትን ችግሮች እንጂ ሌላ ያስገኘው አንዳችም ጥቅም አልነበረውም፡፡

‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› እንዲሉ ዛሬም ቢሆን እዚህም እዛም በሚታየው የጸጥታ ችግር ምክንያት ዳግም የሀገር ሀብት እንዳይባክን፣ የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ፣ አካል እንዳይጎድል እና እንዳይፈናቀል ለማድረግ ነፍጥ ከማንገብ ይልቅ ቁጭ ብሎ ለምክክር ዝግጁ መሆን ብልህነት እንደሆነ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ ላይ ቁጭ ብሎ ለመነጋገር እና ለመወያየት ያሉት ጅምሮችም የሚበረታቱ ናቸው፡፡ በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ሰላም እንዲሰፍን ንግግር እና ውይይት እንዲጎለብት ‹‹ኢትዮጵያ እየመከረች ነው ›› በሚል ሃሳብ ለውይይት ለመቀመጥ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ትልቅ ተስፋን የሚሰጡ ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም ምክክሩ ለይስሙላ ሳይሆን አንዳች የሚያመጣው ለውጥ አለ ብሎ በማመን መንግሥት እንደ መንግሥት፣ ሲቪል ማህበራት፣መገናኛ ብዙኃን የሃይማኖት ተቋማት፣ ምሑራን እና ሌሎችም የሚጠበቅባቸውን ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ምናልባትም በዚህ መንገድ ችግሮችን ተነጋግሮ፣ ፈትቶ ዘላቂ ሰላም ማምጣት ከተቻለ ለሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን ለአህጉሪቱም ምሳሌ እንድንሆን ያደርገናል፡፡ በጦርነት፣በድርቅ በረሃብ፣ በድንቁርና በመሳሰሉት ነገሮች ስሟ ቀድሞ ለሚጠራው አፍሪካ የሚሰጠው አንድምታ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡

ስለዚህም በተለያዩ አካባቢዎች ነፍጥ ያነገቡ ታጣቂዎች በጠብ መንጃ ከማመን ይልቅ በውይይት እና በንግግር ብዙ ችግር እንደሚፈታ አውቀውና ተረድተው ከንግግር በዘለለ በተግባር የታገዘ የሰላም አብሳሪ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፣ሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሠሩ ግለሰቦችም ሆኑ ተቋማት በጦርነት የሚፈታ ችግር እንደሌለ በማመን እና በማሳመን ስለ ሀገር ሰላም ሲሉ የድርሻቸውን የሚወጡበት ጊዜ አሁን እና ዛሬ ነው። ብዙ ተከታይ ያሏቸው ጋዜጠኞችም ሆኑ አክቲቪስቶች የጦር ወሬን በማባባስ እና በማቀጣጠል ‹‹በለው፤ በለው›› ብሎ ወደ እሳቱ ከመገፋፋት ይልቅ ሁሉም ራሱን ገዝቶ ለሰላም በር እንዲከፍት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ጊዜው ዛሬ ነውና እድሉን መጠቀም ብልህነት ይሆናል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



**በቀምሳቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ሳይቃጠል በቅጠል

የእንግሊዘኛው አዲስ ፎርቹን ጋዜጣ በዚያ ሰሞን ዕትሙ አንድ አስደንጋጭ ዘገባ ይዞ ወጥቷል። የትግራይ ክልል ግብርና ቢሮን ጠቅሶ ባስነበበን በዚህ አስደንጋጭ መርዶ አራት መኪና ከእነ ተሳቢው ተመሳስሎ የተሰራ የአፈር ማዳበሪያ መያዙን አርድቶናል። ለፕላስቲክና ለጎማ ምርት ግብዓት የሚሆን የተፈጨ ነጭና ሰማያዊ ላስቲክ ማዳበሪያ ነው ተብሎ ወደ ክልሉ ገብቶ ተይዟል። ይህ ግብዓት ላይ ላዩን ላየው የአፈር ማዳበሪያ ስለሚመስል ነው እንግዲህ ማዳበሪያ ነው ተብሎ ተመሳስሎ የቀረበው። ይህ የተደረሰበትና የተያዘው ብቻ ነው። ምን አልባት ያልተያዘውና ያልተደረሰበት ከዚህ በላይ ሊሆን ይችላል።

ይህ ሕገወጥነት የስንቱን አርሶ አደር መሬት በዚህ ባዕድ ኬሚካል በክሎ ምን አልባትም ለዓመታት መሬቱን ጦም እንደሚያሳድረው፤ ማዳበሪያ ተጠቅሞ ምርት ሊያፍስ ተስፋ ሰንቆ የነበረን አርሶ አደር ተስፋ እንደሚነጥቀው፤ ቤተሰቡንና ልጆቹን ለርሀብ ለእርዛት እንደሚዳርግ ባሰብሁ ጊዜ ለነገ ፈራሁ። ሳይቀጠል በቅጠል ብለን ተረባርበን ነገ ዛሬ ሳንል ካላስቆምነው መዘዙ ዘርፈ ብዙና የከፋ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአፈር ማዳበሪያ ግብይት ላይ የሚስተዋለው ሕገ ወጥ ንግድ ሌላው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ስለሆነ አንዳንድ ነጥቦችን እናንሳ ።

ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱ ሲድህ ሲድህ በማንደራደርበት በሀገራችን የአይን ብሌን ማዳበሪያ ላይ ደርሷል። የሕልውናችን መሠረት፣ የግብርናችን የጀርባ አጥንት የሆነው ማዳበሪያ ላይ እጁን አስገብቷል። መቼም አይደፈርም። አይነካም። አይሞከርም። ብለን በምንተማመነው የማዳበሪያ ግብይትና ስርጭት እጁን ማስገባት ከቻለ ነገ ተቋሞቻችንና መዋቅሮቻችንን እንደማይቆጣጠር ምን ዋስትና አለን። ከጨረታ፣ ከግዥ፣ ከማጓጓዝ እስከ ስርጭት በየደረጃው ባለ የመንግስት መዋቅር ይሳለጣል ብለን በምናምነው የማዳበሪያ ግብይት ካች አምና አምና እና ዘንድሮ ጥቂት ሕገ ወጦች ሲራኮቱበት ታዝበናል።

ከሁለት ሳምንት በፊት 250 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ከስኳር ጋር ተከዝኖ መገኘቱ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱ ምን ያህል እጀ ረጅም እንደሆነ ያሳያል። ስድ የተለቀቀው ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓት ከሕዝባችን 85 በመቶ የሚሆነው ዜጋችን ኑሮውን በመሠረተበት፤ ለሀገሪቱ ጥቅል ብሔራዊ ምርት ድርሻው 47 በመቶ በሆነው ግብርና አንገት ላይ ሸምቀቆውን እያስገ ነው። በጊዜ አደብ እንዲገዛ ካልተደረገ በመሠረታዊው የፍጆታ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይ እንዳደረገው ሸምቀቆውን ስቦ ያንቀዋል። ይህን አደረገ ማለት በ126 ሚሊየን ሕዝብ እና በሀገር ጉሮሮ ላይ ቆመ ማለት ነው። አሁን ባለን የግብይት ስርዓት የማዳበሪያ አቅርቦት በምንም ታምር ከመንግስት እጅ ሊወጣ አይገባም የሚባለው ለዚህ ነው።

በተለይ ከአለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ ያለ አፈር ማዳበሪያ ግብርና የሚታሰብ አይደለም። መሬቱ ማዳበሪያ ለምዷል። ገበሬው መሬቱ ባልጓል። ያለማዳበሪያ በጀ አይልም ይለዋል። ይህን የተረዱ የሕገ ወጥ ግብይቱ ተዋናዮች ገበሬው መሬቱ ጦም ከሚያድር የተጠየቀውን እንደሚከፍል እርግጠኛ ስለሆኑ በግብይት ሰንሰለቱ ሰርገው በመግባት ከሙሰኛ አመራር፣ የልማት ጣቢያ ሰራተኛና ስነ ምግባር ከጎደላቸው ከሕብረት ስራ ማህበራት አመራሮች ጋር በመመሳጠር፤ እንዲሁም አምና ተከስቶ የነበረውን የአቅርቦት መዘግየትና መስተጓጎል

**ዝቅ ብዬ ዋቢ ያደረግሁት አስደንጋጭ ጥናት እንደሚያትተው ደሳሳው ወይም የሕገ ወጥ ግብይቱ ተዋናይ በሀገራችን ለሚስተዋለው የዋጋ ግሽበት 60 በመቶ ድርሻ አለው**

እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም መንግስት በከፍተኛ ድጎማ ለገበሬው ያቀረበውን ማዳበሪያ በሁለትና በሶስት እጥፍ እስከ መቸብቸብ ደርሰው ነበር።

ያለው ውስን ማዳበሪያ በወቅቱ እንዳይከፋፈል በማድረግና ሰው ሰራሽ እጥረት በመፍጠር ቀውስ ፈጥረዋል። ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱ ሀገሪቱ በሌላት የውጭ ምንዛሬ አቅም ከ1 ቢሊየን ዶላር በላይ ወጭ አድርጋ የገዛችውን ማዳበሪያ እንደ ዘይቱና ሲሚንቶው ለመቆጣጠር ዕንቅስቃሴ መጀመሩን ታዝበናል። ባለፈው ዓመት በኦሮሚያ ክልል ከ2 ሺህ 300 ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲዘዋወር መያዙን የክልሉ ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊ መስፍን ረጋሳ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት አስታውቀዋል።

በዚህም ከ2 ሺህ 330 ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ መያዙን፤ በድርጊቱ የተሳተፉ 30 ግለሰቦች በሕግ እንዲጠየቁ መደረጉንም አመልክተዋል። በክልሉ በዘርፉ የሚፈፀመው ሕገ -ወጥነት የአፈር ማዳበሪያ እጥረት ያስከተለ ሲሆን፤ አርሶ አደሮችም ማዳበሪያ በኩንታል እስከ 11 ሺህ ብር ለመግዛት መገደዳቸውን ይታወሳል፡፡ ዘንድሮም እንደአምናው የከፋ ባይሆንም የአፈር ማዳበሪያ ደብቀው በመከዘን የተያዙና በሕገ ወጥ መንገድ ሲያጓጉዙ መያዛቸው ተዘግቧል። የአፈር ማዳበሪያ ከተነሳ አይቀር አንዳንድ ነጥቦችን እናንሳ።

የአፍሪካ አገሮች በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር ሆነው እ.ኤ.አ. በ2006 የአቡጃ ዲክላሬሽን የተባለ አዋጅ ማውጣታቸው ይታወሳል፡፡ አገሮቹ ማዳበሪያን ወሳኝ ስትራቴጂካዊ ሸቀጥ ነው የሚል ዕውቅና ከመስጠት ባለፈ ምርትና አቅርቦቱን ለማሳደግ ቃል ተገባብተው ነበር፡፡ አፍሪካ የማዳበሪያ ማምረቻ ጥሬ ዕቃ ያላት በመሆኗ ምርቱን በማሳደግ ከሌሎች ጥገኝነት መላቀቅ አለባት የሚል ዕቅድ በወቅቱ የያዙ ሲሆን፣ ድንበር ሳይገድበው የማዳበሪያ ንግድ እንቅስቃሴ በስፋት እንዲደረግም ወስነው ነበር። በአቡጃ ዲክላሬሽን መሠረት እ.ኤ.አ. እስከ 2015 ባሉት ዓመታት በአኅጉሩ የማዳበሪያ አጠቃቀምን ከ22 ኪሎ ግራም በሔክታር ወደ 50 ኪሎ ግራም ለማሳደግ ግብ ተይዞ እንደነበር ይታወሳል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ከሰሞኑ በፓርላማ ባቀረቡት ሪፖርት፣ ኢትዮጵያ በአንድ ሔክታር የምትጠቀመውን የማዳበሪያ መጠን ወደ 88 ኪሎ ግራም ማድረስ መቻሏንና የአቡጃ ዲክላሬሽን ግብን ከማንም አገር በተሻለ ማሳካቷን ተናግረው ነበር፡፡ ሚኒስትሩ ይህን ቢሉም የኢትዮጵያ የማዳበሪያ የግብይት ሰንሰለት እንደ ብዙ የአፍሪካ አገሮች በብዙ ችግሮች የተተበተበ ስለመሆኑ በሰፊው ይነገራል፡፡ ኢትዮጵያ ማዳበሪያ ለማምረት የሚያስችል የተፈጥሮ ጋዝና የፖታሽ ማዕድን ክምችት በሰፊው ቢኖራትም እስካሁን ራሷን አልቻለችም፡፡ አገሪቱ በሌላ የውጭ ምንዛሪ እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር በዓመት ማዳበሪያ ከውጭ ለመግዛት ታውላለች፡፡

እ.ኤ.አ. ከ1960ዎቹ ጀምሮ “Freedom from Hunger” በተባለ ፕሮጀክት አማካይነት ማዳበሪያን የለመደው የኢትዮጵያ መሬት፣ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በየዓመቱ ፍጆታውን እየጨመረ መምጣቱ ይነገራል፡፡ በ1970ዎቹ ወደ 3,500 ቶን ማዳበሪያ ነበር የሚገባው፡፡ በ1980ዎቹ መጠኑ ወደ 34 ሺሕ ቶን ሲያድግ፣ ይህ መጠን በ1990ዎቹ 140 ሺሕ ቶን መድረሱ፣ ከዚያም እ.ኤ.አ. በ2012 የአገሪቱ ዓመታዊ የማዳበሪያ ፍጆታ 650 ሺሕ ቶን መድረሱ ይነገራል። በዚሁ ጊዜም አገሪቱ ለማዳበሪያ ግዥ የምታወጣው ወደ 350 ሚሊዮን ዶላር አድጎ ነበር፡፡ከፍ ብሎ እንደተመለከተው አሁን ግን ለማዳበሪያ ግዥ ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ እየዋለ ነው።

ወደ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱ ስንመለስ፤ ከዓመት ዓመት ክንዱ እየፈረጠመ የመጣው ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓት ነገ የሕልውናችንና የሰላማችን ስጋት መሆኑ አይቀርምና መንግስት ነገ ዛሬ ሳይል ስርዓት ሊያሲዘው እና በግብይት ስርዓቱ የሕግ የበላይነትትን ሊያረጋግጥ ይገባል። ካልሆነ እንደ ጣሊያኑ የሲሲሊ ማፍያ በመንግስት ውስጥ ያለ ሌላ መንግስት መሆኑ አይቀርም። መንግስት መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶችን፣ ነዳጅንና ማዳበሪያን በብዙ ቢሊየኖች እየደጎመ በሌለ የውጭ ምንዛሬው ቅድሚያ ሰጥቶ እያስገባ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱ ግን አመድ አፋሽ እያደረገው እና ከሕዝብ ጋር እያቃቃረረው ስለሆነ አበው ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ መንግስት ከዳተኝነት አባዜ ወጥቶ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓቱን በፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ታግዞ ሊያስተከክለው ይገባል።

የግብይት ስርዓታችን ጤናማ ቢሆን ኑሮ የዋጋ ግሽበቱም ሆነ የኑሮ ውድነቱ እዚህ ደረጃ ባልደረሰ። የሀገራችንን የዋጋ ግሽበት የተለየ የሚያደርገውም እሴት በማይጨምሩ ሕገ ወጦች የታነቀ መሆኑ ነው። ይህ ማለት ግን የፍላጎትና የአቅርቦት አለመጣጣም፤ አለማቀፉ የዋጋ ግሽበትና የዩክሬን በራሽያ መወረር ለዋጋ ግሽበቱም ሆነ እሱን ተከትሎ ለመጣው የኑሮ ውድነት አስተዋጾ የለውም ማለት አይደለም። ዝቅ ብዬ ዋቢ ያደረግሁት አስደንጋጭ ጥናት እንደሚያትተው ደላላው ወይም የሕገ ወጥ ግብይቱ ተዋናይ በሀገራችን ለሚስተዋለው የዋጋ ግሽበት 60 በመቶ ድርሻ አለው። መንግስት ይሄን አጉራ ዘለል የግብይት ስርዓት ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ ሳይባባስ አደብ ቢያስገዛ የዋጋ ግሽበቱን 60 በመቶ የመቀነስ ዕድል አለው ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አንድ አስደንጋጭ የጥናት ውጤት ይፋ አድርጓል። ኢትዮጵያ ምግብ ውድ ከሆነባቸው የአፍሪካ ሃገራት ከቀዳሚዎቹ ተርታ መሰለፏንና ከዓለም 8ተኛ ደረጃ፤ ከዚምባቡዌ ቀጥላ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ያለባት ሃገር እንደሆነች አርድቶናል። አጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ 49.1 በመቶ ሲሆን የምግብ የዋጋ ንረት ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ በነገራችን ላይ አሁን ወደ 23 በመቶ እንደወረደ እየተነገረ ቢሆንም ገበያው ላይ የመጣው ለውጥ ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ይህም ከክልል ክልል የተለያየ ሲሆን በአማራና ደቡብ ክልል ያለው የዋጋ ግሽበት ከሃገራዊ ምጣኔው ከፍ ያለ ነው፡፡

ከተቀረው ዓለም የሀገራችንን የኑሮ ውድነት ለየት የሚያደርገው ማለትም ከፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ባሻገር እሴት የማይጨምሩ ደላሎች በገበያ ሰንሰለቱ ከማሳ እስከ ገበያ መሰግሰጋቸው፤ መንግስትም ተገቢውን ቁጥጥርና የእርምት እርምጃ አለመውሰድ የዋጋ ንረቱን አባብሶታል ይላል ጥናቱ፡፡ በዚህም ምክንያት ምርት አምራቹ ከሚሸጥበት 58 በመቶ ዋጋው ከፍ ብሎ ሸማቹ ጋር እንዲደርስ አድርጓል፡፡ ይህ ማለት ዛሬ በሀገራችን ከሚስተዋለው የዋጋ ግሽበት 60 በመቶ ያህሉ የተከሰተው በስግብግብ ነጋዴዎች እና በደላሎች አማካኝነት መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል።

በሕግና በስርዓት ሊስተካከል በሚችል የግብይት ሰንሰለት ሸማቹ ምን ያህል ፍዳውን እያየ መሆኑንም ቁልጭ አርጎ አሳይቶናል። የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከስንት ውትወታ በኋላ ሕገ ወጥ ደላላን ከግብይት ሰንሰለቱ የሚያስወጣ መመሪያ አዘጋጀሁ ቢለንም ስራ ላይ ባለመዋሉ የሀገሪቱ የግብይት ሰንሰለት የደላላ መፈንጫ እንደሆነ ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ በሕገ-ወጥ መንገድ በሚካሄደው የግብይት ስርዓት አገሪቱ በየዓመቱ እስከ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የሚደርስ ገቢ እያጣች መሆኑን፤ በዓለም ታዋቂ ከሆነው የምጣኔ ሀብታዊ መፅሄት “ዘ-ኢኮኖሚስት” ጋር በመተባበር በተዘጋጀውና በአህጉራዊ የንግድ እንቅስቃሴ ችግሮች፣ መንስኤዎቻቸውና መፍትሄዎቹ ዙሪያ በመከረ ጉባኤ ላይ መመልከቱ የችግሩን አሳሳቢነት ያረጋግጣል። በኢትዮጵያ ከሚካሄደው አጠቃላይ የአገር ውስጥ ግብይት ስርዓት ውስ40 በመቶ ያህሉ በሕገ-ወጥ መንገድ በሚገቡ ምርቶች የተያዘ ነው። በዚህም አገሪቱ ከግብይቱ ስርዓቱ ማግኘት የነበረባትን ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በየዓመቱ ታጣለች። ይህ ገቢ ለ72 ሺ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር አገራዊ ኢኮኖሚውን በከፍተኛ መጠን ያግዝ ነበር ተብሏል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ 45 በመቶ የትንባሆ ምርቶች፣ 48 በመቶ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች እንዲሁም 30 በመቶ መድሃኒት በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ በመግባት ገበያውን የሚያውኩት ቀዳሚ ሸቀጦች ናቸው። በዚሁ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓት አማካኝነት ወደ አገር የሚገቡ ጊዜ ያለፈባቸው መድሃኒቶችም የህብረተሰቡን ጤና ስጋት ላይ የሚጥሉ መሆናቸውንም ጥናቱ አመልክቷል።

**ሻሎም !**

**አሜን ።**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# «ወለጋ ላይ የሚመረተው ምርት ለሀገርም የሚበቃ ነው»

- የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ

በሀይሉ አበራ

ኢትዮጵያ ለእርሻ ተስማሚ የሆነ አየር ጸባይና ለም አፈር ባለቤት ነች። በዚህም በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝቧን የምትመግበው ከግብርና ከሚገኝ ምርት ነው። ግብርና አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኑሮ መሠረት ነው። ከምግብ አቅራቦት ባሻገር ለበርካታ ዜጎችም የሥራ ዕድል ይፈጥራል። እንደሀገርም የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ነው።

በግብርና ምርታማ ከሆኑ አካባቢዎች አንዱ የኦሮሚያ ክልል ሲሆን ክልሉ ያለውን የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ቁጥር በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል። በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የሚሆኑ የግብርና ውጤቶችን በማምረት ሀገርንም፣ አርሶ አደሩንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልል ክልሉ እያደረገ ያለው ግብርና እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? የተገኙትስ ውጤቶች እንዴት ይገለጻሉ? ሲል ከኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ ከአቶ ጌቱ ገመቹ ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።



**አዲስ ዘመን - የኦሮሚያ ክልል ትኩረት አድርጎ እየሠራባቸው ያሉትን የግብርና ዘርፎች ቢጠቅሱልን?**

**አቶ ጌቱ ገመቹ-** በአጠቃላይ እንደ ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ከግብርና ሥራዎቻችን አንዱና ትልቁን አድርገን በትኩረት እየሠራንበት ያለው በጋ ላይ የተፋሰስ ልማት፣ ክረምት ላይ ደግሞ የአረንጓዴ ዐሻራው ሥራ ላይ ነው። ይህንኑ ለማሳካትም በጋ ላይ አርሶአደሮቻችን እና አርብቶ አደሮቻችን ትልቅ ትንሽ ሳይቀር በነቂስ ወጥቶ የመሬት ዝግጅት ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል። ባለፉትዓ በአከባባ ጥበቃ ሥራዎችና በአረንጓዴ ዐሻራ በርካታ ትሩፋቶች ተገኝተዋል።

በዚህ ረገድ የሀረማያ ሀይቅ ብዙ ጊዜ በምሳሌነት ይጠቀሳል። ጠፍቶ የነበረው የሀረማያ ሀይቅ አርሶአደሮቻችን በጋ ላይ በመንከባከብ እና በመሥራት የአረንጓዴ ዐሻራውን ሥራም ጨምረውበት ይሠሩ ስለነበረ ሀይቁ እንደገና ተመልሷል። በየቦታውም ኩሬዎች የሚመነጩበት፣ በየቦታው ትናንሽ የውሃ አውታሮች የተገኙበት፣ አርሶአደሮቻችን ደግሞ ከዚያ መጠቀም የጀመሩበት፣ እዛው ከብቶቻቸውን እያደለቡ፣ የወተት ላሞችን እየተንከባከቡ፣ እዛው ንብ እያነቡ ማር የሚያገኙበት እና ትልቅ ጥቅም የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በተጨማሪም በጋ ላይ የምንሸራው የስንዴ ልማት ከላይ የተፋሰስ ልማቱን (የውሃ ሼዱን) ስለምንንከባከብ በቂ ውሃ ከምችት እንድናገኝ አድርጎናል። በአጠቃላይ በጋ ላይ የምንሠራቸው ሥራዎች በዚህ ሀገር ላይ በጣም ትልቅ ልዩነት እያመጣ ይገኛል። ይህም በጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በአረንጓዴ ዐሻራው ላይም ርብርብ በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር እኒሺየቲቭ አድርገው ካስቀመጡበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ በደስታ ይሄንን ሥራ በነቂስ ወጥቶ እየሠራው ይገኛል።

በኦሮሚያ ክልልም በየዓመቱ በደን የሚሸፈነው የመሬት መጠን፣ የምናዘጋጀው ችግኝ በተመሳሳይ እየሰፋ መጥቷል። ለምሳሌ የዘንድሮው ብቻ ሲታይ ወደ አምስት ነጥብ አምስት (5.5) ቢሊዮን ችግኝ ነው ለመትከል አቅደን እየሠራን ነው። በእቅዳችን መሠረትም አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኝ በየቦታው ዝግጁ አድርገናል።

ከዚያም በላይ ዘንድሮውን ለሰው ምግብነት የሚውሉ ችግኞች ላይ ትኩረት አድገናል። ለምግብነት የሚውሉ 500 ሚሊዮን ችግኝ ለማዘጋጀት አቅደን ሠርተን እስካሁን ወደ 490 ሚሊዮን ችግኞችን አዘጋጅተናል። በአጠቃላይም አረንጓዴ ዐሻራው ከምንተክላቸው ችግኝ 11 በመቶውን ለሰው ልጅ ምግብነት የሚሆነውን እንተክላለን ብለን አቅደን እየሠራን ነው ያለነው።

እንደአጠቃላም አረንጓዴ ዐሻራን በተመለከተ ዘንድሮ ወደ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ላይ እንተክላለን ብለን ነው አስበን እየተንቀሳቀስን ያለነው። እስካሁን ድረስ ከ680 ሺህ ሄክታር በላይ ፖሊጎኑ ታስሮለት በጂፒኤስ ጂአይኤስ ተወስዶ የት ምን መተከል እንዳለበት ተለይቷል። ከወዲሁም በአንድ ቀን ተከላ ላይ ማን ምን አይነት ችግኝ የት ቦታ ላይ ይተከላል፣ ምን ያህል ሕዝብ እዛ ቦታ ላይ ይሳተፋል፣ የሚለውን ጭምር ለይተን ተቀምጠናል።

እንደ ኦሮሚያ ክልል ዘንድሮ የራሳችንን ሪከርድ እንዲሁም የሌሎች ክልሎችንም ሪከርድ እንሰብራለን ብለን እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተናል። ለዚህ ደግሞ የኛ አርሶአደሮች እና አርብቶ ለችግኝ ትልቅ ቦታ የሚሰጡ በመሆኑ ያሰብነውን እናሳካለን በለን እናምናለን። በምንሠራባቸው ሥራዎች ልምድ እያገኘንባቸው የመጣንባቸው ሥራዎች አሉ። ለምሳሌ የሞሪንጋ ወይም በተለምዶ ሽፈራው የሚባለው ተክል በተለይ በደቡብ ክልል አካባቢ በስፋት ይታወቃል። ለምግብነት እና ለመድሃኒትነትን ፍቱንነት እንዳለው የሚመሰከርለት ተክል አሁን አረንጓዴ ዐሻራው አካል ነው።

የዘንድሮ ክረምትም ዝናቡ ጥሩ ጊዜ የጀመረበት ነው። የሚዎትሮሎጂ ትንበያ እንደሚያሳየው የዝናብ እጥረት እንደሌለ ገልጸዋል። ስለዚህም እንደ ክልልም ሆነ እንደሀገር ውጤት እናመጣለን ብለን እናስባለን።

በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት ያደረግነው የፍራፍሬ ልማት ነው። በክልሉ ከግብርና ሥራዎች መካከል በትኩረት እየተሠራባቸው ያለው አንዱ ዋናው የፍራፍሬ ልማት ነው ። ከፍራፍሬዎች ደግሞ በጣዕም የተሻሉ እና ወደ ውጭ ኤክስፖርት ሊደረጉ የሚችሉ ፍራፍሬዎች ላይ ነው ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ያለነው።

ከዚህ በፊት እንደሚታወቀው እህልን በክላስተር ነው እየሠራንበት ያለነው። እህልን በክላስተር እንደምሠራው ሁሉ ፍራፍሬ ላይም በክላስተር አድርገን መሥራት እንዳለብን አስበን እየተንቀሳቀስን ነው። ክልሉ ላይ ብዙ አይነት ፍራፍሬዎችን ማልማት ይቻላል። ነገር ግን ለአርሶአደሮቻችን ገቢ ሊያመጡ የሚችሉ፣ የምግብ ይዘታቸው ጥሩ የሆነ፣ የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኙ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን እንገኛለን። ከዚህ ውስጥ አንዱ አቮካዶ ነው።

> **በኦሮሚያ ክልል**
> በሁሉም አካባቢዎች አቮካዶን መትከል እና ማምረት ይቻላል። አቮካዶ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚደርስ የፍራፍሬ ተክል ስለሆነ ሳይንሱን ተከትለን የምንሠራ ከሆነ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንችላለን

በኦሮሚያ ክልል በሁሉም አካባቢዎች አቮካዶን መትከል እና ማምረት ይቻላል። አቮካዶ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚደርስ የፍራፍሬ ተክል ስለሆነ ሳይንሱን ተከትለን የምንሠራ ከሆነ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንችላለን። ይህንኑ መሠረት አድርገንም በክላስተር አድርገን ሰፊ ሥራዎችን እየሠራን ነው ያለነው።

በየዓመቱ በአቮካዶ የሚሸፈነው የመሬት መጠን ሆነ ከአቮካዶ የምናገኘው የውጭ ምንዛሪም በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል። በዘንድሮ 2016 ዓመት በክረምት ችግኝ መትከያ ጊዜ 10 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የአቫካዶ ችግኝ አዘጋጅተናል። በዚህ ዓመት 30 ሺህ ሄክታር መሬት በአቮካዶ እንሸፍናለን ብለን አቅደን እየተንቀሳቀስን ነው ያለነው። በብዛት እየተከልን ያለነው የሀገር ውስጡን አቮካዶ ሳይሆን የተዳቀለውን አቮካዶ ነው ።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## «ወስጋ ላይ የሚመረተው ምርት ...

ከገጽ 7 የዞረ

ሃስ ቫራይቲ (የሀገር ውስጥና የውጭ ዝርያው የተዳቀለበት) አቮካዶ በውጭው ገበያ ጭምር ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ነው። ይሄንን በየዓመቱ ወደ አረብ ሀገር እና አውሮፓ ኤክስፖርት እያደረግን ነው ያለነው። ይሄንን በስፋት አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን - በክልሉ በሩዝ ምርት ላይ ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ ጌቱ ገመቹ -**ሩዝ ኦሮሚያ ላይ ከዚህ በፊት ብዙም አይታወቅም ነበር። ሰብሉ ከኦሮሚያ ይልቅ በአማራ ክልል ፎገራ በሚባለው አካባቢ የበለጠ ይታወቃል። አምና ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ሩዝ ለማልማት አቅደን አንድ ሚሊየኑን ሄክታር በሩዝ አለማንና ወደ 32 ሚሊዮን ኩንታል አካባቢ ልናገኝ ችለናል።

ሩዝ ማምረት ቀላል አይደለም። የተለያዩ ማሽነሪዎች ይፈልጋል። ይህንንም እውን ለማድረግ ወጣቶችን አደራጅተን እንደዚሁም ደግሞ ባለሀብቶችን በዚህ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ውጤት ለማግኘት ተሞክሯል። አሁን ቄለም ወለጋ ላይ ያያችሁት አይነት በሶስት ፤ በሶስት ኪሎ ታሽጎ ለገበያ እየቀረበ ያለው የዚህ ውጤት ነው።

ክልል ሩዝ የማምረት አቅም አለው። ይሄንን አቅም ለመጠቀም በርካታ ርብርቦሽ እያደረግን ነው። በተለይ በዚህ ረገድ ምዕራብ ኦሮሚያ በጣም ትልቅ እንቅስቃሴ ውስጥ ነው ያለው። በተለይ በመኸር ወቅት ላይ ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ ነው ያሉት። ይሄንን ርብርብ በየቦታው ያለው ህብረተሰብ እና ባለሙያ እየደገፈ ከሄደ ብልፅግና ብለን ያስቀመጥነውን ርዕይ በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን እንደምናደርግ እርግጠኛ ነኝ።

**አዲስ ዘመን - በክልሉ ቡና ረገድ ያለው ውጤት ምን ይመስላል**

**አቶ ጌቱ ገመቹ -** እንደ ክልል ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ የቡና ልማት ነው። የቡና ልማት የአሲዳማ አፈርን የሚቋቋም ስለሆነ እዛ ላይ ሰፊ ሥራ በኢኒሸየቲቭ የሚሠራበት ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የቡና ምርታችንን ለማስፋት ብለን በትኩረት እየተንቀሳቀስን ነው።

እንደ ክልል ቡና ምርቱ ብቻ ሳይሆን ጥራቱ ም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣበት ሁኔታን እናያለን። በዘንድሮው ዓመት 11 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ያህል ኩንታል ማምረት ችለናል። ይህም ትልቅ እርካታ ነው።

በሌላ በኩል በጥራት ላይ ትኩረት አድርገን በመሥራታችን ሰፊ ውጤት እያገኘን ነው። ከዚህ በፊት ወደ ውጭ የሚላከው ጥራቱን ያልጠበቀ ቡና ነበር። ብዙ ጊዜም ውድቅ ሆኖ ይመለስ ነበር። ዘንድሮ ግን የቡና ጥራት በመጨመሩ ወደ ውጭ የምንልከው የቡና መጠናችንም ጨምሯል። በውጭ ሀገር ያለው ተቀባይነትም በዚያው መጠን ጨምሯል።

የኛ ቡና ደን አካባቢ ላይ እየተመረተ የሚገኝ ቡና ስለሆነ በኦርጋኒክ ቡናነቱ ነው የሚታወቀው። ከዚህ የተነሳም ቡናው በጣም ተፈላጊ ነው። እኛ ደግሞ ኦርጋኒክነቱን በማስቀጠል ለመሥራት ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራን ነው ያለነው።

አንዱና ዋናውም ችግኝ ጣቢያዎች ለይ የሚሠሩትን ሥራዎች በስፋት መሥራት ነው። ከኬሚካል ንክኪ ነፃ እንዲሆን ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው። ዘንድሮም ወደ ሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ በችግኝ ጣቢያዎች ላይ ለማፍላት አቅደን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ችለናል። ይህም ለዘንድሮው ክረምት አረንጓዴ ዐሻራ ለተከላ ይደርሳል።

ላሎ ቅሌ ወረዳ ላይ እንደሚታየውም ሰፊ ቦታ የሸፈነ በርካታ የነርሰሪ ሳይቶች አሉ። ይህም ለዚህ ክረምት የሚደርስ ነው። ይሄንን ስናደርግ በቡና የሚሸፈነውን የመሬት መጠንንም በዚያው ልክ እንጨምራለን ማለት ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የምርቱንም መጠን በዚያው ልክ እንጨምራለን ማለት ነው። ስለዚህ በሚመጣው ዓመት ላይ ከ12 ቢሊዮን



ወለጋ ላይ ያለውን የአየር ንብረት ከተጠቀምንበት እና የግብርና ሥራውን በሚገባ ከደገፍነው ወለጋ ላይ የሚመረተው ምርት ብቻ ለሀገር በቂ ነው

ቶን በላይ ቡና ለማምረት አቅደናል። በዚህም ለሀገር ውስጥም ለውጭ ገበያም በበቂ መጠን እናቀርባለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በክልሉ በአሲድ የተጠቃ አፈርን ለማከምና ምርታማነት ለመጨመር የሚደረገው ጥረት ምን ይመስላል?**

**አቶ ጌቱ ገመቹ ፡-**የአሲዳማ አፈር መስፋፋት አንዱ የክልላችን ችግር ነው። በምዕራብ ወለጋ ችግሩ የባሰ ነው። በምስራቅ ወለጋም ቢሆን ችግሩ አለ። በምዕራብ ወለጋ በተለየ መነሲቡ ወረዳ በአሲድ ክፉኛ ተጠቅቷል።አሲድ ብቻ ሳይሆን ምስጥም በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል። እነዚህ ሁለት ነገሮች የመሬትን የምርታማነት መጠን እየቀነሱት መጥተዋል ። አንዳንድ ቦታ ላይ ሙሉ ለሙሉ ምርት የማይሰጥ ቦታ አለ። ቀይ አፈር ሆኖ ሳር እንኳን ማብቀል ያልቻለ ቦታ አጋጥሞናል ።

ስለዚህም የአፈርንም ምርታማነት ማሳደግ ጊዜ የሚሰጠው ተግባር አይደለም። በተለይ ምዕራብ ወለጋ ላይ ሰፊ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው። ይሄ አካባቢ የቡና ምርትም የሚገኝበት በመሆኑ ትኩረት ሰጥተን መሥራት አለብን። አንዳንድ ተክሎች አሲዳማነትን የመቋቋም ባህሪ ስላላቸው እነሱን በስፋት የመትከል እቅድ አለን። አሲዳማነት የመቋቋም ባህሪ ካላቸው ተክሎች አንዱ ቡና ነው። ሻይ የአሲዳማነት ባህሪን የመቋቋም ባህሪ አለው፣ አቦካዶም እንዲሁ አቅም ያለው ተክል ነው።

በአሲዳማ አፈር አካባቢ የተተከለው አቮካዶ የተራቆተውን አፈር በአረንጓዴ ቀይሮ አንድ ሄክታር ከማይሞላ ቦታ ሁሉ ወደ 60 ኩንታል ያህል ወደ ውጭ መላከ የተቻለበት አንዱ ማሳያ ነው። የዚህ አካባቢ አፈርን ለማከም ከተፈለገ አቮካዶ ላይ መረባረብ ያስፈልጋል።

እንደ ኦሮሚያ ክልልም ዓይናችንን ወደ ዚህ ማዞር አለብን ብለን ነው የያዝነው። አሁን ባየነውም በፊትም ባለን መረጃ መሠረት እዚህ አካባቢ ላይ ሰፊ ሥራ መስራት የምንችለው አቮካዶ ላይ ነው። አቮካዶ ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥተን ከሠራን ይሄ መሬት ይታከማል።

ይህም ሌላ መረጃ ማምጣት ሳያስፈልግ በተግባር የታየው ነው።

ስለሆነም አርሶ አደር ጋር የአቮካዶ ችግኝ በሰፊው ካቀረብንለት አርሶአደሩም ያንን ተጠቅሞ መሬቱን ያክማል ማለት ነው። አርሶ አደሩ ባዶ በነበረው መሬት ላይ አቮካዶ ከተከለ ከሶስት ዓመት በኋላ የአቮካዶ ምርትን ከሀገር ውስጥ አልፎ ወደ ውጭ መላክ ይችላል ማለት ነው።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ደግሞ አርሶ አደሩ ወደ አግሮ ፕሮሰሲንግ የሚገባበትን መንገድ እያመቻቸን እንሄዳለን። በዚህም ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች በመንግሥት በኩል ማበረታቻ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በጸጥታ ችግር ውስጥ የነበሩት የምዕራብ ወለጋ ዞኖች አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ጌቱ ገመቹ ፡-** የምዕራብ ወለጋ ዞን ወዳዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት ከመልማት ተከልክለው የቆዩ ናቸው። የፌዴራልና የክልል መንግሥት በተሰጠ አቅጣጫ መሠረት በተለይ የግብርና ቢሮ ከምዕራብ ወለጋ ዞን ጋር በቅርበት በመሥራት ላይ ይገኛል ። አቮካዶ እና ሙዝ ወደ ውጭ መላክ የተጀመረ በመሆኑ በወረዳዎቹ የሚደረገው የልማት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል የሚል እምነት አለን። የተለያዩ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችም ከተሟሉ ምርቶቹን ተከትለው ወደ አካባቢው ይመጣሉ ብለን እንጠብቃለን።

ባሳለፍነው ስድስት ቀናት ወለጋ ላይ ያለውን የልማት አቅም ያየንበት ሁኔታ ነው ያለው። ይሄ አካባቢ ትልቅ የልማት አቅም ያለው አካባቢ መሆኑን የሚዲያ ሰዎችን ጨምሮ ሁላችንም በአካል በመገኘት ያየነው ነው። እዚህ አካባቢ ያለው ህብረተሰብ ለልማት ትልቅ ተነሳሽነት ያለው ህብረተሰብ እና ልማት ላይ እየተሳተፈ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። በተለይም በዚህ በመኸር ወቅት አርሶ አደሩ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ መሆኑን ታዝበናል።

አጠቃላይ በወለጋ አካባቢ ላይ በተደረገው የሥራ ጉብኝት ህብረተሰባችን በሁሉም ቦታዎች ላይ ያለውን የልማት ጥማት ተመልክተናል። የልማት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን በትክክልም ሥራ ውስጥ ገብቶ እየሠራ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ሕዝቡ ተነቃቅቶ ወደ ልማት ወደ ሥራ ገብቷል ። በሁሉም ዞኖች አመርቂ ሥራዎች እየታዩ ነው። ለአብነትም የታጣቂዎች መፈንጫ የነበረው የቄለም ወለጋ ዞን የታየው ልማት ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው።

በሌማት ትሩፋቱም ጥሩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት። የቡና ተከላ ጅማሬውም የሚያስደስት ነው፤ ለወደፊቱም የህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል። በአጠቃላይ ወለጋ በልማት ላይ ነው ያለው፤ ወለጋ ልማትን እየተጠማ ሕዝብ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተአምራዊ ለውጥ እንደሚያመጣ እርግጠኛ ነኝ። በተለይም በየደረጃው ያለው የመንግሥት መዋቅር አካባቢውን ከደገፈው ለሌሎችም ዞኖች የሚተርፍ አቅም እንዳለው ተገንዝበናል።

ወለጋ ላይ ያለውን የአየር ንብረት ከተጠቀምንበት እና የግብርና ሥራውን በሚገባ ከደገፍነው ወለጋ ላይ የሚመረተው ምርት ብቻ ለሀገር በቂ ነው። ይህም ለንግግር ብቻ ሳይሆን በአካል ማንኛውም ሰው መጥቶ ሊያረጋግጠው የሚችለው ነው። ወለጋ ላይ አንድ ነገር ተተክሎ ወዲያው የሚበቅልበት፣ የሚያደግበት አፈር ነው ያለው። በአንድ በኩል ከዝናብ መብዛት ጋር ተያይዞ አሲዳማነት ቢያጠቃቸውም በሌላ በኩል ደግሞ በጣም ለም አፈር እንዳለ በዚህ ዙሪያ ላይ ለመመልከት ችለናል።።

ስለዚህም ወለጋ ውጤታማ እንዲሆን ሌሎች ሴክተሮችም ዓይናቸውን ከዚህ አካባቢ መንቀል የለባቸውም። ሕዝቡም ወደ ልማተ እየገባ ስለሆነ ሕዝብ የበለጠ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አፈላጊ ነው። ይህን ማድረግ ከተቻለ በአጭር ጊዜ ውጤት ይመጣል፤ እንደሀገርም ተጠቃሚ እንሆናለን።

**አዲስ ዘመን -ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ**

**አቶ ጌቱ ገመቹ -** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የኃይል አቅርቦትን ያሻሻለው ሀገራዊ ንቅናቄ

**አንተነህ ቸሬ**



በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው ግብዓቶች መካከል አንዱ የኃይል አቅርቦት ነው፡፡ በቂና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት የሌለው ሀገር ስለአምራች ዘርፍ እድገት ሊያስብ አይችልም፡፡

ዛሬ በአምራች ዘርፍ እድገት በዓለም አቀፍ ደረጃ በአርዓያነት የሚጠቀሱት ሀገራት ለኃይል ልማት ከፍተኛ ትኩረት የሰጡ በቂና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን እውን ማድረግ የቻሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ አስተማማኝና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለአምራች ኢንዱስትሪው እድገት የጀርባ አጥንት ነው።

ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ዘርፍ እምቅ አቅም ያላት ሃገር ብትሆንም፣ በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ የሆኑት የዘርፉ ችግሮች ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ያህል ጥቅም እንዳታገኝና ከረጅም ዓመታት በፊት ጀምሮ ሲነገርለት የቆየው መዋቅራዊ የምጣኔ ሃብት ሽግግር እስካሁን ድረስ እንዳይሳካ እንቅፋት ሆነዋል፡፡ ከሀገሪቱ የአምራች ዘርፍ ማነቆዎች መካከል አንዱ የኃይል አቅርቦት እጥረት ነው፡፡ ይህ ችግር አምራቾች ባሰቡት ልክ እንዳያመርቱ በማድረግ በምርት መጠን፣ በስራ እድል ፈጠራ እና በውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ የኃይል እጥረቱ አምራቾቹ ማሽኖቻቸውን ብቻም ሳይሆን የሰው ኃይላቸውንም በበቂ መጠን እንዳይጠቀሙ አድርጓቸዋል፡፡

በፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዘርፍ የሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች በአምራች ኢንዱስትሪው ውስጥ ስላላቸው ሚና ይፋ ባደረገው ጥናት፤ ምንም እንኳ መንግስት ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተለየ ማበረታቻና ድጋፍ ፓኬጆች አዘጋጅቶ ወደ ስራ የገባ ቢሆንም፤ አብዛኛው የሀገር ውስጥ የግል ባለሀብት የመጀመሪያ ምርጫው አምራች ኢንዱስትሪው ሳይሆን የንግድ፣ ሪል እስቴትና የአገልግሎት ዘርፎች እንደሆኑ አመልክቶ ነበር፡፡

ለዚህ ደግሞ ጥናቱ በምክንያትነት የጠቀሳቸው ቀድመው በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ አብዛኛዎቹ ባለሀብቶች የኃይል እጥረትን ጨምሮ በብዙ ችግሮችና ማነቆዎች ምክንያት ውጤታማ ባለመሆናቸው ወደ ዘርፉ መግባት ለሚፈልግ ባለሀብት ጥሩ አርአያ መሆን አለመቻላቸውን እና በንግድና አገልግሎት ዘርፎች የሚገኘው ትርፍ በጣም የተጋነነና ሳቢ መሆኑን ነው፡፡

የሀገሪቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥማቸውን የኃይል እጥረት ለማቃለልና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል። የውሃን ጨምሮ የነፋስ፣ የእንፋሎትና የነፋስ ኃይል ማመንጫዎች ተገንብተዋል፤ የኃይል መሰረተ ልማት ዝርጋታዎች እንዲሻሻሉ ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ሥርጭትና አቅርቦት ለማሻሻል የሚያግዝ ስምምነት ባለፈው ዓመት ተፈራርመው እንደነበርም ይታወሳል፡፡

ስምምነቱ በዋናነት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ሥርጭትና አቅርቦትን ማሻሻል ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ስምምነቱ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ወደ ማምረቻ ኢንዱስትሪው በስፋት ገብተው በዘርፉ የሥራ ዕድል ፈጠራን፣ የኤክስፖርት ምርትና ገቢን ለማሳደግ የሚያስችላቸውን እድል እንደሚፈጥር እንዲሁም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ሂደት ውስጥ የሚገጥሙ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት እና የኃይል አቅርቦት ከመቋረጡ አስቀድሞ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ተገልጾም ነበር፡፡ በእነዚህ ጥረቶች የማይናቁ ውጤቶች ቢመዘገቡም፤ ከአገሪቱ አቅምና ከችግሩ ስፋት አንፃር ግን መፍትሄዎቹ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊያስገኙ እንዳልቻሉ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል አንዱ የሆነው «ኢትዮጵያ ታምርት» ሀገራዊ ንቅናቄ፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚጋጥማቸውን የኃይል አቅርቦት ችግር በማቃለል ረገድ ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ መንግሥትም ሆነ አምራቾች ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ስራ አስፈፃሚ ኢንጂነር አሸብር ባልቻ «ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የኃይል አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት ከፍተኛ እገዛ እያደረገ እንደሚገኝ ይገልፃሉ፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፣ ንቅናቄው የተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚያቀላጥፍ በመሆኑ፣ ከዚህ ቀደም በኃይል አቅርቦት ረገድ ይስተዋሉ የነበሩ የቅንጅት ጉድለቶችን ለማረም የሚደረገውን ጥረት እያገዘ ይገኛል፡፡

«የኃይል አቅርቦትና የአምራች ዘርፍ ስራ ከፍተኛ ትስስር አላቸው፡፡ ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ለኃይል ዘርፍ ልማትም ወሳኝ ግብዓቶች ናቸው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል አምራች ኢንዱስትሪው ምርት ለማምረት ያስችላል፤ የአምራች ኢንዱስትሪው ምርቶች ደግሞ ለኃይል ምርትና ስርጭት ግብዓት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ስለሆነም ምርት ማምረት ያለኃይል አቅርቦት እንዲሁም ኃይል ማምረትና ማቅረብ ደግሞ ያለኢንዱስትሪ ምርቶች ሊታሰቡ አይችሉም» በማለት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትና የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት ተግባር ጠንካራ ትስስር እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

ኢንጂነር አሸብር እንደሚሉት፣ «ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ስራ እንዲጀምሩ እንዲሁም ነባሮቹም የማምረት አቅማቸው እንዲጨምር በማድረግ ተጨማሪ ኃይል አቅርቦት ፍላጎት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ንቅናቄው የኃይል አቅርቦት ፍላጎቶች በባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት ምላሽ እንዲያገኙ እድል ፈጥሯል፡፡

የኃይል አቅርቦትና ስርጭት ተግባር ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ ኃይል ለማምረትና ለአምራቾች ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጥር እንደሚችል ኢንጂነር አሸብር ስጋታቸውን ይገልፃሉ፡፡

«በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከምታመነጨው ኃይል 96 በመቶ የሚሆነው ከውሃ የሚመነጭ ነው፡፡ ሀገሪቱ ከፀሐይ፣ ከእንፋሎትና ከነፋስ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችልም ከፍተኛ አቅም አላት፡፡ ከሀገሪቱ አቅም እና የመልማት ፍላጎት አንፃር በርካታ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ያስፈልጋሉ፡፡ የዘርፉ ልማት ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል፡፡» ሲሉ ያብራራሉ፡፡

« የኃይል ማመንጫዎች እድሜያቸው ሲጨምር እድሳት ይፈልጋሉ፤ ካልታደሱ ውጤታማነታቸው ይቀንሳል፡፡ ግንባታቸውም እድሳታቸውም ከፍተኛ ወጭ አለው፡፡ እስካሁን የተሰሩት ስራዎች ወጭ የተሸፈነው መንግሥት በመደበው ከፍተኛ ገንዘብ ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የአገልግሎት ክፍያ በቂ ስላልሆነ ታሪፉን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ታሪፉን ማሻሻል የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራት ያሻሽላል፤ የግል ባለሃብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ያበረታታል» ይላሉ፡፡

ከታሪፍ ማሻሻያው በተጨማሪ በመንግሥትና የግል አጋርነት አሰራር (Public-Private Partnership) የግሉን ዘርፍ በኃይል ልማት ዘርፍ ማሳተፍ እንደሚገባም ኢንጂነር አሸብር ይመክራሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሽፈራው ተሊላ በበኩላቸው፣ ንቅናቄው ለአምራች ኢንዱስትሪው ካስገኛቸው አወንታዊ አበርክቶዎች መካከል አንዱ በኃይል አቅርቦት ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮችን በተቀናጀ አሰራር ለማቃለል የሚቻልበትን እድል መፍጠሩ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ የንቅናቄው ትግበራ በኃይል አቅርቦት ረገድ ተስፋ ሰጭ ውጤቶች እንደተመዘገቡበት ይገልፃሉ፡፡

አቶ ሽፈራው እንደሚሉት፣ አገልግሎቱ በልዩ ትኩረት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ዋናዎቹ ለአምራች ዘርፉ ጥራት ያለውና አስተማማኝ የሆነ ኃይል ለማቅረብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ለአዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ተደራሽ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ለኢንዱስትሪ ደንበኞች ቅድሚያ የሚሰጥ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህ የኢንዱስትሪ ደንበኞች ልዩ ትኩረት የሚያገኙበት አሰራር በቴክኖሎጂ እንዲታገዝም ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የደንበኞች ግንኙነት ስርዓት እንዲሻሻል ከማድረግ በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ደንበኞች የተለየ የጥሪ መስመር (904) ተዘጋጅቷል፡፡

«በአሁኑ ወቅት ከ8200 በላይ ከተሞችና መንደሮች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በ96 ትልልቅ ከተሞችና የኢንዱስትሪ ማዕከላት በሆኑ አካባቢዎች የኃይል መሰረተ ልማቶችን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ የኃይል አቅርቦቱ በብዙ አካባቢዎች ተደራሽ በመሆኑ ኢንዱስትሪዎች በጥቂት አካባቢዎች ብቻ ተከማችተው እንዳይገኙ አዎንታዊ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትም እየተሻሻለ ነው፡፡ የአምራቾችና የአገልግሎቱ ስራዎች የተሳሰሩ ናቸው፡፡ አምራቾች ለምርት ስራዎቻቸው ኃይል እንደሚፈልጉ ሁሉ አገልግሎቱም ስራዎቹን ለማከናወን ከኢንዱስትሪ ደንበኞች የሚጠቀማቸው ብዙ ግብዓቶች (ኬብሎች፣ ትራንስፎርመሮች...) አሉ» በማለት የኃይል አቅርቦትንና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል ስለሚከናወኑ ተግባራት ያብራራሉ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ የኃይል አቅርቦት ከአምራች ዘርፉ ተወዳዳሪነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ይናገራሉ፡፡ «ለአምራች ዘርፉ እድገት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የኃይል ልማትና ስርጭት ወሳኝ ናቸው» የሚሉት አቶ ታረቀኝ፣ መሰረተ ልማትን በማስፋፋት የተመረተውን ኃይል ወደ አምራች ኢንዱስትሪዎች በማድረስ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት መፍጠር በ«ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ በልዩ ትኩረት እንደሚከናወን ይገልፃሉ፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ መጠናከር ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚያሳድግ ግብዓት ነው፡፡ ለአብነት ያህል የግብርና ምርታማነትን ለመጨመር ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎችን እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉን ውጤታማነት ለማሻሻል ደግሞ የዘርፉን የስራ እንቅስቃሴ የሚያሳልጡ ግብዓቶችን (መሳሪያዎችን) በብዛት፣ በጥራትና በፍጥነት የሚያመርት አምራች ዘርፍ ያስፈልጋል፡፡ አምራች ዘርፉ ከሚጠናከርባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ግብዓቶችን ማሟላት እንዲሁም አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ነው፡፡

የኃይል አቅርቦት ከግብዓቶቹ መካከል ወሳኝ ሚና አለው፡፡ አማራጭ ኃይልን በመጠቀም ለኢንዱስትሪዎች ያልተቆራረጠ ኃይል ማቅረብ ይገባል፡፡ የአባይ ግድብ የኃይል አቅርቦት ችግሩን በመፍታት ረገድ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ብዙ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

አንዳንድ ሀገራት የድንጋይ ከሰል ሀብታቸውን አጋዥ አድርገው በመጠቀማቸው ምርቶቻቸውን አምርተው ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ ስለሆነም ያልተቆራረጠ ኃይል ለማቅረብ የድንጋይ ከሰል አማራጮችን ማጤንና መጠቀምን ችላ ማለት አያስፈልግም፡፡ የኃይል አቅርቦት ችግሩ መፍትሄ ካገኘ አምራቾች በአቅማቸው ልክ ማምረት የሚችሉበት እድል ይፈጠራል፡፡

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች እንዳሉ አይካድም፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት የሚመጣጠኑ በመሆናቸው ለወቅቱ የሚመጥን ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ የአምራች ዘርፉን ችግሮች መፍታት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ የመፍትሄ አቅጣጫ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የአምራች ዘርፉን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የዘርፉ አጠቃላይ አሰራር የሚመራባቸውን አስፈላጊ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና በብቃት መተግበር ይገባል፡፡

## ጎሜ

# እኛስ ከከተማዋ ጋር ምን ያህል ዘምነናልን?

**እስማኤል አረቦ**

አዲስ አበባ በእርጅና ብዛት ጎብጣ መነሳት ከተሳናት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከተሰሩ ዘመናትን የተሻገሩት ደሳሳ ጎጆዎቿ እርጅና ተጭኗቸዋል። በጉያዋ ያሉ ቤቶች ግድግዳዎቻቸው ፈራርሶ፤ ጣራዎቻቸው ወይቦ አዲስ አበባን ከዕድሜዋ በላይ አስረጅተዋታል፡፡

ቤቶቹ ሰዎች ይኖሩባቸዋል እንጂ ከንፋስም ሆነ ከፀሃይ እንዲሁም ከዝናብ ማንንም አያስጥሉም፡፡ በበጋም ሆነ በክረምት በእነዚህ ቤቶች ውስጥ መኖር ስቃይ ነው፡፡ በተለይም በመሃል የከተማዋ ክፍል የሚገኙት ቤቶች ከተማዋ ስትቆረቆር ጀምሮ የነበሩ በመሆናቸው ለመፍረስ አንድ ሀሙስ ብቻ ነበር የቀራቸው፡፡

ፒያሳና እና አራት ኪሎን የመሳሰሉ መሃልኛው የአዲስ አበባ ክፍል ችምችም ብለው በተሰሩ ቤቶች የታጨቀ፤ ከዘመኑ ጋር ያልዘመነ፤ ከ130 ዓመታት በፊት በነበረው የቀጠለ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን የአኗኗር ሁኔታ የማይመጥን ነው፡፡

ፒያሳን የመሳሰሉ አካባቢዎች ስማቸው ገናና ቢሆንም በገቢር ግን ስማቸውን የሚመጥን ገጽታ የላቸውም፡፡ ምንም አይነት ዘመናዊነት የማይታይባቸው ኋላቀር አካባቢዎች ከመሆናቸውም በላይ በስመ አራዳ ለዘመናት ድህነት ተጭኗቸው የቆዩ ናቸው፡፡

ዛሬ ግን የ137 ዓመት የእድሜ ባለጸጋዋ አዲስ አበባ መልኳን እየለወጠች ነው፡፡ አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴ መናኸሪያ እንደ መሆኗ ይህን የሚመጥን ልማት እየተከወነላት ይገኛል፡፡

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች ባማረ መልኩ እየተሰሩ ነው፡፡

በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያከለው ኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሰረቱ የሚቀይር ነው፡፡ የተሽከርካሪ መሄጃ አስፋልቱን እና የእግረኛ መንገዱን ስፋት ለተመለከተውም ዓለም አቀፍ ደረጃን ባሟላ መልኩ እየተገነባ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ‹‹አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በአፍሪካ ካሉ ዋና ከተማዎች ከኬፕታውን በስተቀር የሚወዳደራት ከተማ እንደማይኖር በተግባር የምናሳያችሁ ጉዳይ ነው፡፡›› ሲሉ አዲስ አበባ እንደስሟ ውብ እና አዲስ የምትሆንበት ጊዜ መቅረቡን ተናግረዋል፡፡

ይኸው ጉዳይ አሁን በተግባር እየተገለጸ ነው። ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ ያሉት መንገዶች እጅግ ባማረ ሁኔታ ተገንብተዋል፡፡ ዛሬ ፒያሳንና አራት ኪሎን የተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን እስኪጠራጠር ድረስ መገረሙ አይቀሬ ነው። የአስፋልቱ ጥራት፤ የእግረኛ መንገዶቹ ስፋትና ጥራት፤ የመናፈሻዎቹ እና አረንጓዴ ስፍራዎቹ ውበትና ድምቀት፤ የዘንባባዎቹ ማራኪነት በሙሉ እጅን አፍ ላይ ለመጫን የሚያስገድዱ ናቸው፡፡

ለወትሮው በአቧራና በእርጅና ብዛት ተጎሳ ቁለው የነበሩ ሕንጻዎችና ፎቆች ዛሬ ታድሰው አዲስ ሙሽራ መስለዋል፡፡ በየስርቻው ተወትፈው የነበሩ ቅራቅንቦዎች ተወግደው የፒያሳና የአራት ኪሎ ውበት ወለል ብሎ እንዲታይ ሆኗል፡፡ ብዙዎች እሪ ይሉበት የነበረው እሪ በከንቱም ዛሬ ስሙን አድሶ ሰላምና ውበት ፈሶበታል፡፡

አፍን በሚሰነፍጥ ሽታው የሚታወቀው ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ ያለው መንገድም ጽዳቱ ተጠብቆለታል፤ ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶችም ተገንብተውለታል፡፡ በአጠቃላይ በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት ዓለም ከደረሰበት የዘመናዊ ከተማ መስፈርት አንጻር አዲስ አበባም መሰለፍ ጀምራለች፡፡

> የእኛዎቹ አሽከርካሪዎች ግን ከዘመናዊነት በተፋታ መልኩ ዛሬም መኪናቸውን በሰፋፊ ጎዳናዎች ላይ ከማቆም ባህል አልተላቀቁም፤ ከዘመናዊነት ጋር አልተዋወቁም

ሆኖም ከአዲስ አበባ መዘመን ጋር እኛ ነዋሪዎቿ ምን ያህል ዘምነናል ? ወይም ለመዘመን ተዘጋጅተናል? የሚለው ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ነው።ይህንን ጥያቄ ልናነሳ የቻልነው ደግሞ ከልማቱ ጎን ለጎን የታዘብናቸው ጉዳዮች ስላሉ ነው፡፡

የመጀመሪያው ጉዳይ የጽዳት ጉዳይ ነው፡፡ አንዲት ከተማ ዘመናዊ የሚባለው ወይንም ደግሞ ነዋሪዎቿ ዘምነዋል የሚባሉት ለጽዳት ትኩረት ሲሰጡ ነው፡፡ ጽዳት ዘመናዊነት መገለጫ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እየዘመነች ባለችው ከተማ በተቃራኒ ከተማዋን የሚያቆሽሹና ውበቷን የሚያጎድፉ ተግባራት አሁንም ይስተዋላሉ፡፡

ውብ በሆኑት እነዚህ ጎዳናዎች በየቦታው የሚሸኑ ሰዎች አጋጥመውኛል፡፡ እንኳን ለመሽናት ቀርቶ ለመራመድም በሚያሳሳው ጎዳና ያለምንም ሀፍረት ቆመው የሚሸኑ ሰዎች ዛሬም አልጠፉም፡፡

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፤ የአፍሪካ መዲናና ከኒዮርክና ጄኔቫ ቀጥላ ሶስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ በየሜዳው መጸዳዳት እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ከተሞች ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መቀመጫነት ሊመረጡ የሚችሉት ጽዱና ውብ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡ ጽዱና ውብ ያልሆኑ ከተሞች ለማንኛውም አገልግሎት ተመራጭ አይሆኑም። ስለዚህም ከ50 ዓመታት በላይ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ሆና የቆየችው አዲስ አበባ በጽዳቷ ምክንያት መቀመጫነቷ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ባዶ ሜዳ ላይ መጸዳዳትና አካባቢን መበከል በርካታ የሆኑ ውስብስብ ችግሮችን የሚያስከትል ነው፡፡ ባዶ ሜዳ ላይ የሚጸዳዳ ማህበረሰብ ክብር የለውም፡፡ የሰው ልጅ ተደብቆ ወይም ተከልሎ ከሚያደርጋቸው ተግባራት መካካል አንዱና ዋነኛው መጸዳዳት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ሲሆን ክብርን ያጎድፋል፤ ከሰው ልጅ ተርታ አስወጥቶ ከእንስሳት ተርታ ያሰልፋል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ አብዛኞቹ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች የተቀበሩት ከከተማዋ ምስረታ ጋር በተያያዘ በመሆኑ ከማርጀታቸውም ባሻገር አሁን ያለውን የሰው ቁጥር የማስተናገድ አቅም ለማስተናገድ የሚያስችሉ መጸዳጃ ቤቶች አልነበሩም፡፡ በዚህም ላይ በየጊዜው በሚሰሩ ግንባታዎች አማካኝነት ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎቹ ለብልሽት ስለተዳረጉ በአግባቡ ፍሳሽን የማስወገድ አቅም አልነበራቸውም፡፡

በዚህም ምክንያት አካባቢዎቹ በየጊዜው በሚፈነዱ መጸዳጃ ቤቶች የሚጥለቀለቁና አፍንጫ በሚሰነፍጥ ጠረናቸውም የሚታወቁ ናቸው። አግባብ ባይሆንም ሰዎች የቆሸሹትን የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ለማቆሸሽ ብዙም ሞራል ጥያቄ የሚያነሳባቸው አልነበረም፡፡

ዛሬ ግን ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶች እየተገነቡ ነው። ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ ባለው ኮሪደር እንኳን ከ20 የማያንሱ መጸዳጃ ቤቶች እየተገነቡ ነውለ። ስለዚህም በየቦታው መጸዳዳት በተለይም አሁን ባለው ሁኔታ ከአዲስ አበባ ዘመናዊት ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡ ስለዚህም እየዘመነች ካለችው ከተማ ጋር አብሮ ለመጓዝ እራስን ማስተካከል ይገባል፤ በየቦታው መጸዳዳትም ነውር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ከዚሁ ከጽዳት ጋር በተያያዘም ሶፍት፤ ወረቀት፤ የውሃ መያዣ ፕላስቲክ (በተለምዶ ኃይላንድ) የመሳሰሉትን በየቦታው መጣልም ከእንግዲህ ወዲያ በቃ ሊባል ይገባል፡፡ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ከእንግዲህ ወዲያ አበቦችንና አትክልቶችን እንጂ ቆሻሻዎችን መሸከም አትችልም፡፡ ስለዚህም ቆሻሻዎችን እየተዘጋጁ ባሉ የቆሻሻ ማስቀመጫዎች ውስጥ በመጣል የከተማዋን ጽዳት መጠበቅ የሁሉም ነዋሪ ግዴታ ሊሆን ይገባል፡፡

ሌላው እየዘመነች ያለችውን ከተማ ውበቷ እንዳይጎላና ጎዳናዎቿ እንዳያምሩ እንቅፋት እየሆነ ያለው ተሽከርካሪዎችን በዘፈቀደ ማቆም ነው፡፡ ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ ያለው ሰፊ ጎዳና መኪኖችን እንደልብ የሚያንሸራሽርና ለመኪናዎች መቆሚያም የራሱ የሆነ ፓርኪንግ ታስቦ የተሰራለት ነው፡፡

ሆኖም ከቀድሞው ባህል ያልወጡ አሽከርካሪዎች በየቦታው መኪናቸውን በመገተር የትራፊክ ፍሰቱን ሲያስተጓጉሉና እነሱም ለቅጣት ሲዳረጉ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ በየትኛውም ዓለም ቢሆን ከመኪና መቆሚያ ውጭ እንደፈለጉ አቁሞ መሄድ የሚፈቀድ አይደለም፡፡ የእኛዎቹ አሽከርካሪዎች ግን ከዘመናዊነት በተፋታ መልኩ ዛሬም መኪናቸውን በሰፋፊ ጎዳናዎች ላይ ከማቆም ባህል አልተላቀቁም፤ ከዘመናዊነት ጋር አልተዋወቁም፡፡

በእግረኞች በኩል የሚታዩ ክፍተቶች ደግሞ በሰፊው እና ባማረ መልኩ የተሰሩ እግረኛ መንገዶችን ትቶ በመሃል አስፋልት መጓዝ አሁንም ያልተላቀቀን አባዜ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ሲከናወን ለእግረኛ መንገዶች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በርካታ ሰዎችን አዝናንቶ እንዲጓዙ የሚያደርጉ ስፋታቸው ከ10 ሜትር ያላነሱ የእግረኛ መንገዶች ተገንብተዋል፡፡ እነዚህ መንገዶችም በአበቦችና በዘንባባ ዛፎች ያጌጡ ናቸው፡፡ ሆኖም አንዳንድ እግረኞች ይህን ያማረ ቦታ ለቀው አስፋልት ውስጥ ሲጓዙና እራሳቸውንም ለአደጋ ሲያጋልጡ ተመልክተናል፡፡

በትራፊክ አደጋ ዙርያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት እስከ 84 በመቶ የሚደርሱ አደጋዎች የሚከሰቱት ከእግረኞች ጋር በተያያዘ ነው። ይህ ደግሞ እግረኞች የተፈቀደላቸውን መንገድ ትተው የተሽከርካሪ መስመር ውስጥ በመግባታቸው የሚፈጠር ችግር ነው፡፡

በእርግጥ ቀደም ሲል አብዛኞቹ መንገዶች ሲሰሩ የእግረኛ መንገዶችን ታሳቢ አድርገው ስለማይሰሩ በቂ የእግረኛ መንገዶች አልነበሩም፡፡ ስለዚህም እግረኞች አስፋልት ውስጥ ገብተው ለመጓዝ ይገደዱ ነበር፡፡

በእግረኛ መንገዶች አለመኖር ሳቢያ የሚደርሰውን አደጋ የሚተነትን ጥናታዊ ጽሁፍ ይፋ እንዳደረገው በአዲስ አበባ አምስት ሺሕ 784 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው መንገዶች የተገነቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል ኹለት ሺሕ አምስት መቶ 39 ኪ.ሜ ብቻ የአስፋልት መንገዶች እንደሆኑና ከአስፋልት መንገዶች 35 በመቶ ብቻ የእግረኛ መንገዶች ሲኖራቸው እነርሱም ከፍተኛ ጥገና የሚፈለጉ ናቸው።

የትራፊክ አደጋን ከሚያስከትሉ ጉዳዩች መካከል የእግረኛ መንገድ አለመኖር ከፍተኛውን ሚና እንደሚወስድ በዚህም በተለያዩ ጊዜ ከሚደርሱት አደጋዎች መካከል 84 በመቶ የሚሆነው የሚደርሰው አደጋ እግረኞች ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በዚህም በ2010 በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ከደረሰ የትራፊክ አደጋ ሦስት ሺሕ አራት መቶ 59 መካከል በእግረኞች ላይ የደረሰ አደጋ ኹለት ሺህ ዘጠኝ መቶ 14 እንደሆነና ከዚህ እግረኞች በእግረኛ መንገድ ላይ ሲጓዙ አራት ነጥብ አራት በመቶ፣ የእግረኛ መንገድ በሌለበት ግራቸውን ይዘው ሲጓዙ 10 በመቶ እንዲሁም የእግረኛ መንገድ በሌለበት የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዘው በመጓዛቸው የደረሰ አደጋ 4 አራት ነጥብ ስምንት በመቶ መሆኑንም በጥናቱ አመላክተዋል።

ዛሬ ግን ይህ ችግር ተቀርፏል፤ በቂ የእግረኛ መንገዶች ተሰርተዋል፡፡ ስለዚህም አንድ እግረኛ የተፈቀደለትን መንገድ ለቆ አስፋልት ውስጥ ገብቶ እንዲሄድ የሚያደርገው አስገዳጅ ሁኔታ የለም፤ አያድርገውና አደጋ ከተከሰተም ጥፋቱ የእግረኛው ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

በአጠቃላይ እየዘመነችው ካላችው ከተማ ጋር አብሮ ለመጓዝ ዘመናዊ አስተሳሰብና ተግባራት ያስፈልጋሉ፡፡ በተለይም ከጽዳት፤ ከፓርኪንግ እና ከእግረኛ መንገድ አጠቃቀም ጋር ያሉ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ማስወገድና ከዘመኑ ጋር አብሮ መጓዝ የግድ ይላል፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ከአድማስ ባሻገር

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ሀሳቤን አገልድሜ ከአድማስ ማዶ ሽቅብ ብወጣ አንድ ነገር ታየኝ። ጸጉሩ ጥቁር የሀር ጥጥ የመሰለ፣ አፍንጫው እንደ ጎበዝ ወታደር ቀጥ ብሎ የቆመ ሰልካካ... በረዶ ከሚያስንቁ ጥርሶቹ የሚወጣው የፈገግታ ጸዳል ለልብ ሀሴትን ይቸራል። የአዕምሮ ምጥቀቱን ግን በቃላት ላኤጠው ያልቻልኩት ጥልቅ ውቅያኖስ የመሰለ ሶታ ጎረምሳ ጎምላልዬ ወጣት ከወደኋላኛው ዘመን ታየኝ።

ውበትን ከደም ግባቱ ችሮት ሳያንሰው መግነጢሳዊ የአዕምሮ ምጥቀትና ልህቀትን ከጥበብ ጋር ሲሰጠው እግዜሩም ለእርሱ ብቻ ያዳላ መስሎ ተሰማኝ። ነገሩ ቅናት አንጨርጭሮኝ ምቀኝነት አብግኖኝ አልነበረም። የህይወት ግርማ ሞገሱ ልቤን ቢያቀልጠው እንጂ። እግዜር ይህን ሁሉ ሰጥቶት ሲያበቃ እድሜውን ግን ለምን እንደዘነጋው አልገባኝም፡፡ አንድ ታላቅ ጀብዱ ፈጽሞ እንዲመለስ እንጂ በምድር ላይ ሽብቶ በከዘራ እንዲንዛዛ አልፈቀደለትም፡፡ እናም ይበልህ ሲለው አመጸኛና ሞገደኛ ጸሀፊ አደረገው።

የብዕሩ አንደኛው ጫፍም ከላይ የሚመዘዝ ይመስለኛል። የሚጽፈው ብቻም ሳይሆን እርሱ እራሱ ትንግርት ነው። የብዕሩም ጫፍ ለገባው የላም ጡት፣ ለጠላቶቹ ደግሞ ሳማና እሬት ነው፡፡ እንደለመደው በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች፣ እንዲሁም በመነን መጽሔት ታንኩን ከመድፉ ሲያገላብጥ አንድ ቀን ግን አንጠልጥለው ለፍርድ አቀረቡት፡፡ አንድ ብቻውን ሆኖ በብዕሩ ሀገር ምድሩን የሚያናውጠው አመጸኛውን ከሥራ አግደው ጋዜጣና መጽሔቱን ለዓይኑ እንዲናፍቅ አደረጉት፡፡ ከደሞዙም ላይ ጎማመዱበት፡፡ ሥራ የፈታ ቀውላላ ሆነ። የዚህን ጊዜ አወጣ አወረደ። እኔ የመጣሁበት ትልቁ ዓላማ በጋዜጣና መጽሔት ብቻ የሚቆም አይደለም ብሎ አሰበ፡፡ በደማቋ ውብ ጨረቃ ከመስኮቱ ላይ ቆሞ አሻግሮ ከአድማስ ማዶ ቢመለከት... ”ከአድማስ ባሻገር” የተሰኘች አንዲት ዓለም ታየችው፡፡

በ1962 ዓ.ም ወጣቱ በዓሉ ግርማ የበኩር ሥራው የሆነችውን “ከአድማስ ባሻገር”ን ጽፎ አስነበበ፡፡ ዛሬ የምንመለከታትም ይህችኑ የመጽሐፍ ዓለም ነው፡፡ በክረምቱ ዝናብ የወንዙ ሙላት ሳይሞላ፣ የጨረቃዋም ጀንበር ሳትጠልቅ ተሻግረን ልንቃኛት ወደድን፡፡

አብዛኛዎቻችን በዓሉን የምናስታውሰው የሞትን ጽዋ ከተጎነጨባት ከ”ኦሮማይ” ጋር ነው፡፡ ነገር ግን፣ የታላቅነቱ ቁልፍ የተንጠለጠለባት መጽሐፍ “ከአድማስ ባሻገር” ናት ብለው ሚሞግቱም ጥቂት አይደሉም። ልክ ሀዲስ አለማየሁ ብለን “ፍቅር እስከ መቃብር” እንደምንለው ማለት ነው። ይሁንና ደራሲው የበሰለው በልምድ ብቻ ሳይሆን ገና ከመጀመሪያውም የብዕር ሱናሚ ያስነሳው ሞገደኛ ስለመሆኑ “ከአድማስ ባሻገር” ይነግረናል፡፡ መጽሐፉ የሁሉም የበኩር መክፈቻው ሲሆን፣ ከእርሱ መጽሐፍት መካከል በውጭ ቋንቋ ተተርጉሞ የተጻፈ ብቸኛው መጽሐፍም ነው።

ብዕሩ እንደ ግዙፉ የመድፍ ቀለሀ ነው። በጻፈ ቁጥር ይተኩሳል። በተኮሰ ቁጥርም ጠላቶቹን እያሸበረ አንባቢውንም የሚያወዛግብ ጭምር ነው። “ከአድማስ ባሻገር” አርቆ የተመለከተበት አርቆም ያሰበበት ድንቅ ሥራው ነው፡፡ በብዙ ገጾች ባይገጠገጥም በብዙ ሀሳቦች የተደጎሰ ረዥም ልቦለድ ነው፡፡

የገጸ ባህሪያቱ ሞገደኛነት ከራሱ ይወለዳል፡፡ አስተሳሰብንም ሆነ ሀገርና ሕዝብ ወዳድነቱን የሚማሩት ከራሱ ከደራሲው ነው። በእውን የሚወልዳቸው እንጂ በምናብ የሚፈጥራቸው አይደሉም። ለአብነትም “የቀይ ኮከብ ጥሪ” በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ዋና ገጸ ባህሪው “ሲራክ” ከየትም የመጣ ሳይሆን ስብሐት ገ/ እግዚአብሔር ነበር። እርሱን አስፈቅዶ ስብሐትን ከነቃጭሉ ዱብ አደረገበት። ወደዚህኛው መጽሐፉችን ስንመጣ ደግሞ “አበራ ወርቁ” የተሰኘው ዋናው ገጸ ባህሪ እራሱ በዓሉ ግርማ ነው። የሁለቱን መመሳሰል በጥቂቱ ብንመለከተው እንኳን፣ የአበራ መላው አስተሳሰብና ፍላጎት ከበዓሉ ጋር ልክክ ብሎ የሚገጥም ነው።

እንደ ትዝታ ሁለቱም በዊንጌት ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረዋል። ዲግሪያቸውንም የጫኑት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በመበጠስ ነው። ከዚያ ወዲያም ወደ አሜሪካን ይጓዙና በጋዜጠኝነት ላይ የፖለቲካ ሳይንስ አክለው ይመረቃሉ። እኚህ ሁለቱ ትንግርቶች ሥራ የሚይዙትም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ነው። መንቲያ ላለመምሰል ግን በአንዲት ነገር የተስማሙ ይመስላል፡፡ በዓሉ ግርማ ሞገደኛ ጸሀፊ፣ አበራ ደግሞ የስነ ስዕል ከራማው የሚያይልበት ዓይነት ነው።

ከአድማስ ባሻገር ላይ ያለው የአበራ የኑሮ ትዕይንት ገና በገጽ አንድ ሲጀምር፣ “ቤቱን የዝምታ አዘቅት ውጦታል። ከዚያ ዝምታ... ከዝምታ የሚመነጨው የሙዚቃ ቃና መጨረሻ የለውም፡፡ ነብስን ከሀሴት ሊያወራጭ፣ አዕምሮን ኮርኩሮ ሀሳብን በስልት ሊያስደንስ ይችላል፡፡ አበራ ወርቁ በዚያ መጨረሻ በሌለው ዝምታ ተውጦ ሙሉውን የሌሊት ልብሱን ለብሶ እንደልማዱ የጣት ጥፍሩን በጥርሱ እየከረከመ ወዲህና ወዲያ በመንጎራደድ ለገላው ያሞቀው ውሀ ወደ ገንዳው እስኪወርድለት ድረስ የወትሮ ባልሆነ ትዕግስት ይጠባበቃል፡፡

...ትኩስ የሕይወት ጠብታ፣ ትኩስ ወፍራም የሕይወት ጠብታ የሚል ሀሳብ ለአንድ አፍታ በአበራ አዕምሮ ውስጥ ብልጭ ብሎ መልሶ ድርግም አለ፡፡ የአበራ አዕምሮ ከአንድ ሀሳብ ወደሌላ ሀሳብ እንዳሻው ስለሚጋልብ አንድ ነገር ላይ በተለይ ጊዜ ወስዶ እስከመጨረሻው ድረስ ሊያስብ አይችልም፡፡ ለዚህ ነበር ባለቅኔ ወይንም ደራሲ ወይንም ሰዓሊ የመሆን ተስፋውን ውስጡ ቀብሮ ያስቀረው፡፡ ነብሱ ግን እራሷን በአንድ ነገር ለመግለጥ ዘለዓለም እንደዋተተች፣ እንደቃተተች ትኖራለች፡፡” በማለት ይጀምራል፡፡

የአበራ የስዕል ተሰጥኦ አንገቱን በመዳፏ ጨብጣ ሲጥ ልታደርገው ምንም አልቀራትም፡፡ እርሱም በእርሷ መሸነፉን አውቆ የምትፈልገውን ሁሉ ሊሰጣት ፈልጓል። ግን ደግሞ የመንግሥት ሥራውን አቋርጦ ሊካድማት ቢያስብም፣ በመወሰንና ባለመወሰን ገመድ ታንቋል፡፡ በሌላ በኩል የትምህርት ቀለም ያልነከረው ታላቅ ወንድሙ አባተ ሚስት የማግባት ሩጫ ላይ ተጠምዷል፡፡ ልፋቱ እያለከለከም ጭምር ነው፡፡ ቀናኢ ፍቅር ያለው በጎ ሰው ቢሆንም ልጅ የማግኘቱ ነገር ግን ከላይ የታዘዘለት አይመስልም፡፡ ብዙ ሚስት ቢያገባም ከአንዱም ጠብ የሚል ልጅ ጠፋ፡፡

መቼም ከእግዜሩ ጋር ግብ ግብ ባይፈጥርም በስተመጨረሻ ግን ለተስፋ መቁረጥ እጅ ወደመስጠት አድልቷል፡፡ አሁን ያለው አንድ ተስፋ አበራ ብቻ ነው፡፡ ዓይኑን በዓይኑ ለማየት ባይችልም የወንድሙን ልጅ የማየት ጽኑ ምኞት አድሮበታል፡፡ በበዛው ቤተሰባዊ ፍቅራችን ውስጥ እንኳንስ የወንድምና የአጎትና የአክስት ልጅም ከራስ የማይቆረጥ ስጋ ነበር፡፡ ያኔ “...ዘመድ እስከ አክስት” ሳይሆን በፊት፣ መወለድ ቋንቋ በነበረበት ጊዜ፡፡ እናም አባተ፣ አበራ ሚስት አግብቶ ልጅ እንዲወልድ እሳቱን ይቆሰቁሰዋል፡፡ ቢሆንም ኃይለማርያም የተባለው የአበራ የልብ ጓደኛ እሳቱ ላይ ንፋስ እያስገባ ጥረቱን የሚያከስም እየመሰለው አይነ ውሀም ደስ አይለውም፡፡ በመሀል ግን ሉሊት ጎምላሌዋ እየተዘናከተች ከተፍ አለች፡፡ ሱዛናም ከትዝታው ጋር ብቻ ትኖራለች፡፡ ለትዳር ተቆልፎ ሲንቀዋለል የነበረው የአበራ ልብ በአንዴ ተከፈተ፡፡

የተማረ ሰው እቅድና ሂደት ይወዳል፣ ሁሉን ቦታ ቦታ አሳክቼ ቀስ ብዬ አገባለሁ ብሎ የሚያስብ የነበረ ቢሆንም ሉሊትን ወዷታልና እንድታመልጠው አልፈለገም፡፡ ከዚያም በፍቅር እሳት ነደው የትዳር ጎጆ ቀለሱ፡፡ አባተ በልቡ ስንቱን ታቦት ተስሎ የተገኘ ነገር ነውና የተሰማው ጥልቅ የደስታ ስሜት ወደሌላው ሰውም የሚዛመት ነበር፡፡

ከላይ እንደጠቀስነው አበራ በዚህች ምድር የመኖሩ ትርጉምና የሕይወት ደወል ጥሪው ከስዕል ጥበብ ላይ እንዳረፈ እርግጠኛ ነው፡፡ ወደፊት ለመራመድ አንድ ባለ ቁጥር ከፊቱ እንደጅብራ የሚቆመው ፈተና ግን ከመንገዱ ውልፍት አላደርግ ብሎታል፡፡ ችንካሩን ለመንቀል በተነሳ ቁጥር አንገቱን አስግጎ እያፈጠጠ የሚመጣበት ይብሳል፡፡ በጊዜው ለነበረው ስርዓት የእርሱ ተሰጥኦ ደንታም የሚሰጠው እንዳልሆነ ያስባል፡፡ ከእርሱ ሕይወት የምናገኘው የታሪክ ጭብጥ በብዛትም ፖለቲካው በዘረጋው ወጥመድ ውስጥ እየወደቁ ያሉትን ባለተሰጥኦ ወጣቶችን ሕይወት የሚያሳይ ነው፡፡

በትዕይንት የተሞላውን የገጸ ባህሪያቱን ታሪክ ደራሲው አሰባጥሮ ያስቀመጠበት መንገድ ልዩ የሆነ ስዕላዊ ምስልን የሚከስቱ ናቸው፡፡ የእያንዳንዱ ገጸ ባህሪያት የታሪክ ፍሰት ከምስላዊ ትዕይንቱ ጋር ሲታይ በዝምታ እንደሚወርድ ወራጅ ወንዝ የሚማርኩ ናቸው፡፡ መጽሐፍ እያነበብን ሳይሆን ከመሳጭ የቲያትር መድረክ ጋር የተፋጠጥን ይመስለናል፡፡ በዓሉ ያለውን እምቅ የጥበብ ጉልበት እንድናይለት ያደረገበት ሌላኛው ነገር በትንሽ ቃላት ውስጥ ብዙ ስሜቶችን መሰነግ መቻሉ ነው፡፡

አንድን ስሜት ለመረዳት አሊያም ለማስረዳት ቃላት ሲዘንቡ ነበር የምናውቀው፣ “ከአድማስ ባሻገር” ግን በእንዲህ ለመቆም አልፈለገም፡፡ ከምናነባቸው ከእያንዳንዱ አራት ነጥቦች በመለስ፣ ከነገረን ውጪ ውስጣችንን የሚሰረስሩን ሌላ ተጨማሪ ስሜቶችን ይልክብናል፡፡ የትዕይንቱ ግለት የገጸ ባህሪያቱ ላይ ታች ማለት በጉጉት ቆንጥጦ በተመስጦ እየመዠለገን ያቁነጠንጠናል፡፡ ገጸ ባህሪያቱ ከዓይነ ህሊናችን፣ ትዕይንታዊ ስሜቱ ደግሞ ከልባችን ሰፍረው ለማሰላሰል እንኳን ፋታ አይሰጡንም፡፡ በቃላት ከሚፈሰው ታሪክ ይልቅ በድርጊት የተሞላው እንቅስቃሴ ስሜታችንን እንዲጠልፈው አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ ምሁራኑም “ሜሎድራማቲክ” ይሉታል፡፡ ልብ አንጠልጥል፣ ልብ ሰቅዝ በመሆኑ ነው፡፡ ታዲያ እኚያ ሁሉ እያነበብን የተጋራናቸውና የተዛመቱብን ስሜቶች ሁሉ ይህችን ከምታህል በጥቂት ገጾች ከተደጎሰች መጽሐፍ ውስጥ ስለመሆኑ ያጠራጥረናል፡፡ እንግዲህ የማይጋፋትን ጥበቡን ሰጥቶታልና እኛም ስንቀምስ ዝም ብለን አምነን ማጣጣም ካልሆነ በቀር እንዴትስ በዓሉን ላለማድነቅ ይቻለናል...

ከአድማስ ባሻገር ካለችው የመጽሐፍ ጎጆ ውስጥ አለፍ ብለን ወደ ገጽ 72 ስንሻገር የሚለን ይህንን ነው፣

“...እነሱ እነሱ የምትሉት እነማን ናቸው? እኛስ እነማን ነን? እነሱ እነሱ ከማለት ራሳችንን ዞር ብለን እንመልከት፡፡ ወደኛ ዞር ብንል የምናየው ምንድነው? ወኔ ቢስ አታሞዎች ሆነን እንገኛለን፡፡ ከካስቲል ወይም ከኢትዮጵያ ሆቴል ስንወጣ፣ ለማኞች ላይ እያገሳን የምናልፈው እኛው ነን፡፡

...

ለሀገር ልማት ይህን ያህል ከደሞዛችሁ ስጡ ብንባል መጀመሪያ የምናለቅሰው እኛው ነን፡፡ መንግሥት ጀርባ ላይ እንደ ቱሀን ተጣብቀን የምንኖረው እኛው ነን፡፡ ከሞግዚት ጉያ ወጥተን፣ በሁለት እግራችን መቆም ያስፈራናል፡፡ በራሳችን ላይ እምነት የለንም፡፡ ማንነታችንን አናውቅም፡፡

....እንደኛ ያሉት ሰዎች በየትኛውም መንግሥት ስር ያው ናቸው፣ ከማማረር አያልፉም፡፡ ...ግን እስከመቼ?”

ከዚህች ከአንዲት ገጽ ውስጥ ከተቀነጨበ ጽሁፍ ላይ እንኳን የበዓሉን የፖለቲካ ጓዳ ወለል አድርጎ ያሳየናል። ፍትህና እውነትን ፍለጋ የሚሞግተው መንግሥትን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም ጭምር ነው፡፡ ሽንጡን ገትሮ ሲቆም በምክንያት እንጂ በጭፍን የስሜት ጨለማ ውስጥ ተውጦ አይደለም። ለመንግሥትም ሆነ ለተለያዩ አካላት ጥላቻ የለውም፣ እውነትን ሲጋርዷት ግን ብዕሩ የሚያነድ የእሳት እረመጥ ነው። የልቡን እንጂ ልወደድ ባይ ቅቤ አንጓችነት አይታይበትም። የ“ኦሮማይ” የሞት በቅሎ አስደንብራ ነብሱን ከገደል ብትጨምረውም፣ ገና “ከአድማስ ባሻገር” ሳይወለድ ጀምሮ ጠላቶቹ ብዙ ነበሩ፡፡ “ከአድማስ ባሻገር”ም ታማኝ ጠላቶችን አላፈራለትም ለማለት አይቻልም፡፡ ነገሩን በውል አስተውሎት ለማሰብ ቢቃጣኝ ጊዜ አንዲት ሀሳብ ሽው! አለችብኝ፡፡ በዓሉ መጽሐፍ የመጻፍ ችሎታ እንዳለው ገና በፊትም ያውቅ ነበር፡ ፡ ለዚህ የሚሆን ሀሳብም ጠፍቶበት አነበረም፡፡ የመረጠው ግን አሳቻ ጊዜ እየጠበቁ በጋዜጣና መጽሔቱ ላይ መጻፍን ነበር፡፡ አንድ የሚጠብቀው ጊዜ እንደነበረም ተሰማኝ፡፡ ጠብቆም ጊዜው ሲደርስ “ከአድማስ ባሻገር”ን ጻፈ፡፡ ከዚህ በኋላ የነበሩትን ቀሪ አምስት መጽሐፍት ለመጻፍ የፈጀበት ጊዜ ግን ከአሥር ዓመት ያልበለጠ ነበር። እናም የገጠመልኝ ሀሳብ ቢኖር፣ በዓሉ የሕይወት ጥሪውን ብቻም ሳይሆን ጠላቶቹ አኮብኩበው የሚጠብቋትን የእስትንፋሱን የመቋጫ ቀንም አስቀድሞ ያውቃት የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ይመስለኛል ለራሱ ከንቱውን ሕይወት ኖሮ አንዳችም ሳያጎድል እያከታተለ ሁሉንም ሰጥቶን መሄዱ፡፡

የበዓሉ ግርማን መጽሐፍቶች ባነበብን ቁጥር በእያንዳንዱ ውስጥ አንዲት ጀብዱ መራሽ የሆነች ሴት አናጣም። እኚህ ሞገደኛ ሴት ገጸ ባህሪያት ወንዱንም ጀግና ሁሉ የሚያርበደብዱና ያሻቸውን ነገር ከማድረግ የማይዛነፉ ብርቱዎች ናቸው፡፡ እኚህን የሴት አብዮተኞች በዚህን ያህል ደረጃ ለማስቀመጥ የፈለገበትን ምክንያት ኖሮ ብንጠይቀውና ቢመልስልን እንዴት ደስ ባለን...በ”ኦሮማይ” መጽሐፉ ውስጥ ያለችውን ፊያሜታ ጊላይን እናስታውሳለን፡፡ እዚህ “ከአድማስ ባሻገር” ደግሞ ሉሊት አለች፡፡ ከጎሊያድ ጎራዴ ይልቅ እንደ ዳዊት ጠጠር ስትወነጨፍ እንመለከታታለን፡፡ ይህን ያህሉን በራስ መተማመን ከወዴት እንደምታመጣው ያስገርመናል። ሱዛናም ሌላኛዋ ናት፡፡ ሴትነት ከምንም ነገር ሊያጎድል የማይችል፣ የአዕምሮ እንጂ የተፈጥሮ ዳገት አለመሆኑን ደራሲው ነግሮ ሳይሆን አሳይቶ ያሳምነናል፡፡

ከአድማስ ባሻገር የነበረው የመጨረሻ አድማስ በበርካታ ውጥንቅጦች የተሞላ ነው፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረው የትዕይንቱ ግለት ተጧጡፎ ሌላ ሆኗል፡፡ አበራ ለሉሊት ያለው ፍቅር ባይቀዘቅዝም ከልቡ ውስጥ ሹክ ያለውን ሰይጣን ጆሮ ዳባ ለማለት ግን አልቻለም፡፡ ቅናት የልቡን በር ሰብሮ አንጨረጨረው፡፡ ልበሙሉነቷ ከውስጧ የሚንጎማለልባትን ሉሊትን በሌላ ወንድ ጠረጠራት፡፡ የገባበትን ጥርጣሬ እያባባሰ የሚያቀጣጥለው ነፉስ እንጂ የሚያረግብለትን የስሜት ውርጭ አጣ፡፡ ትንሽዬ ሆና ከውስጡ የበቀለችውና እንደ ፓራሳይት የተጣበቀችው ቅናት፣ የፍቅር ደሙን እየመጠጠች ወፍራና ደልባ አረፈችው፡፡ ይህን ጊዜ ከፉ ከፉውን ሆነ ዓይነህሊናው የሚቃርመው፡፡ መጨረሻህ አይመር ሲለው ሾተላዩን አንስቶ የሞት አንካሴውን ጨብጦ የፍቅሬ ተኩላ ነው ብሎ ሲጠረጥረው የነበረውን ሰው ገደለው፡፡ የሰውየውን ነብስ ወደ ገነት ይሁን ወደ ሲኦል ሸኝቶ እሱም በዚያው ወደ ከርቸሌ ወረደ፡፡ ታላቅ ወንድሙ አባተም ስህተትን በስህተት ለማረም ገባ፡፡ በአበራ ለደረሰው ነገር ሁሉ ጥፋተኛው ያ ወትሮም ቀልቡ ያልወደደው ጓደኛው ኃይለማሪያም እንደሆነ እርግጠኛ ሆነ፡፡ በተራ ፍላጻውን አንስቶ ወደ ኃይለማሪያም ገሰገሰ፡፡ እስትንፋሱንም ጸጥ እረጭ አሰኛት፡፡ ገደለው፡፡ ቀጥሎም የሞት ጽዋውን ለራሱ ተጎነጨ። እራሱንም ደገመና አብረው አሸለቡ፡፡

ሁሉም ሰው የሞትን ባህር ተሻግሮ ከመሄድ አይቀርም፡፡ ሁሉም ሰው ግን እንዴት ይሆን የሚሻገረው? በዓሉ ስድስቱን መጽሐፍቶቹን ጨምሮ ሌላ አንድ መጽሐፍም አለው፡፡ 7ኛው ግን እራሱ ነው፡፡ እሱም ያለው ከእኛው ውስጥ ነው። ይህንንም ከቀሪ መጽሐፍቶቹ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡



ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የምልክት ቋንቋ መስማት ከተሳናቸው ባለፈ

**እየሩስ ተስፋዬ**

የተለያዩ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አይደሉም ተብለው በተደጋጋሚ ወቀሳ ይቀርብባቸዋል። የጉዳት ዓይነታቸውን ያማከለ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በስፋት ባለመኖራቸው እንደዜጋ ማግኘት ያለባቸውን ግልጋሎት ሳያገኙ ይቀራሉ። በዚህ ምክንያት ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከሌሎች ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ተሳትፏቸው አናሳ ሆኗል።



የብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ችግራቸውን ሊያቃልል የሚችል እና የተቋሙን ጥረት በዚሁ ይቀጥል የሚያስብለውን ሥራ ከሰሞኑ ሠርቷል። አገልግሎቱ ‹‹ኢትዮጵያን ሴንተር ፎር ዲስኤቢሊቲ ኤንድ ዴቨሎፕመንት›› ከተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመሆን ለአገልግሎት ሰጪ ሠራተኞቹ መሠረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና እንዲያገኙ አድርጓል።

የአገልግሎቱ የዋና ዳይሬክተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አባተ ካሳሁን እንደሚገልጹት፤ ተቋሙ መስማት የተሳናቸውን ጨምሮ ለሌሎች አካል ጉዳተኞች አካታች የሆነ አገልግሎት በስፋት እየሰጠ ነው ለማለት ያዳግታል። ከዚህ ቀደም ለዓይነ ሥውራን ብቻ የተዘጋጀ ቦታ የነበረ ቢሆንም አገልግሎቱ አካታች ነው ከመባል ይልቅ አግላይነት የታየበት በመሆኑ ሊታረም ችሏል። በአሁኑ ወቅት አካታች የሆኑ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። ተቋሙ አሁን የጀመረው መልካም ተግባር እንደ ተቋም ለብዙ መስማት ለተሳናቸው ዜጎች ለመድረስ ዕድል የሚሠጥ ነው። ለሰልጣኞችም ተጨማሪ እውቀት እና የሥራ ዕድል መፍጠር ይችላል።

በተለያዩ ተቋማት ላይ በምልክት ቋንቋ አገልግሎት መስጠት ቢቻል ጥቅሙ ብዙ ነው። ለአብነት የሕክምና ተቋማት እና መሰል ተቋማት የግድ የምልክት ቋንቋ የሚችሉ ባለሙያዎች ያስፈልጋቸዋልና፤ እንዲህ ያለው ተስፋ ሰጪ ሥራ ቀጣይነት ቢኖረው ብዙ ችግሮችን ማቅለል ይቻላል። ሌሎች ተቋማትም እንዲህ ባለው ሥራ በመሳተፍ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኙ ቢደረግ የሚያበረታታ ነው።

የብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ዳይሬክተር ወይዘሮ ሀገሬ መኮንን በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ተቋሙ መሠረታዊ የምልክት ቋንቋ ትምህርትን ለሠራተኞቹ በመስጠት ለሌሎች ተቋማት አርዓያ የሚሆን ተግባር አከናውኗል። ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም መስማት ለተሳናቸው ዜጎች በተገቢው መንገድ የሚያገለግልና በምልክት ቋንቋ በሚገባ ማስረዳት እና መግባባት የሚችል ሠራተኛ ያስፈልጋቸዋል።

አገልግሎቱ ላለፉት ሰማንያ አንድ ዓመታት ንባብ እንዲስፋፋ እየተጋ ያለ ተቋም ነው። አገልግሎቱን ለመስጠት ግን ዋናው ነገር መግባባት ነው። ይህንን ታሳቢ በማድረግ በየጊዜው የክህሎት ስልጠናዎችን በመስጠት በተለይም ተማሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ብዙ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። በቀጣይም ተቋሙ ከብሔራዊ ቴአትር ሠራተኞች ጋር አብሮ በመሥራት ቴአትሮችን በምልክት ቋንቋ እንዲተረጎሙ አድርጎ ለዕይታ እንዲበቃ አስቻይ ሁኔታዎች ይመቻቻል።

የ‹‹ኢትዮጵያን ሴንተር ፎር ዲስኤቢሊቲ ኤንድ ዴቨሎፕመንት (ECDD) ዋና ዳይሬክተር ጌታሁን ስምኦን (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚሉት፤ በዓለም ጤና ድርጅት እና በዓለም ባንክ እ.ኤ.አ በ2011 በተጠናው ጥናት መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ 15 በመቶ ወይም አንድ ቢሊዮን ሰዎች፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ20 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸው እንደሆኑ ጥናቶቹ ይፋ አድርገዋል። እነዚህ አካል ጉዳተኞች አብዛኞቹ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙ፣በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና በሌሎች ችግሮች የተገደቡ ናቸው። ይባስ ብሎም ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑት አካል ጉዳተኞች በመሥሪያ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ይሁኑ እንጂ ሥራ የሌላቸው በመሆኑ የችግሩን አሳሳቢነት ያሳያል።

መንግሥት እነዚህን የኅብረተሰቡ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ አሉታዊ አመለካከቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። አካል ጉዳተኞች ልክ እንደ ጉዳት አልባ ዜጋ በልማት እና በሌሎች ፕሮግራሞች ተካታች እንዲሆኑ የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይገባል።

ከዚህ ባለፈ የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማሳደግ ፖሊሲዎች፣ አስቻይ ሕጎች እና የተለያዩ መርህ ግብሮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ያሉትን ፖሊሲዎችና ሕጎች ተግባራዊነታቸው እንዲረጋገጥ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ማኅበረሰቡ ከፍተኛ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል ።

አካል ጉዳተኞች የማኅበረሰቡ አካል እንደመሆናቸው በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት የተጀመረው መልካም ጅማሮ በፍትህ ተቋማት፣ በህክምናው እንዲሁም እንደ ማኅበረሰብ እያንዳንዱ ሰው መሠረታዊ የመግባቢያ ምልክቶች በተገኘው አጋጣሚ መማር እና ልዩ ፍላጎት ካላቸው ዜጎች ሀገሪቱ በሁሉም ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን ተግባቦት ላይ አብሮ መሥራት ያስፈልጋል ።

የአገልግሎቱ ሠራተኞች የምልክት ቋንቋ ሰልጥነዋል። ባገኙት እውቀት እና ክህሎት አካታች የሆነ አገልግሎት እንዲኖር የሚያስችልና ባለሙያዎቹ መስማት ከተሳናቸው ተጠቃሚዎች ጋር እንዲግባቡ ብሎም መረጃ እንዲለዋወጡ ያስችላቸዋል። እንዲህ ያለውን በጎ ጅምር ሌሎች ተቋማት እንደ አርአያ ወይም ምሳሌ በማድረግ ለብዙዎች መድረስ እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

# ዓለም አቀፍ



## በኩዌት የውጭ ሀገር ሠራተኞች መኖሪያ ሕንጻ ላይ በደረሰ የእሳት አደጋ ከ40 በላይ ሰዎች ሞቱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኩዌት ከተማ በሆነችው ማንጋፍ ውስጥ በሚገኝ አንድ የመኖሪያ ሕንጻ ላይ በደረሰ የእሳት አደጋ ቢያንስ 41 ሰዎች መሞታቸውን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተጋሩ ቪዲዮዎች የሕንጻው የታችኛ ክፍሎች በእሳት ነበልባል ሲቃጠሉ፣ ከላይኛው ክፍሎች ደግሞ ጥቁር ጭስ ሲወጣ አሳይተዋል።

ባለሥልጣናት እንዳሉት፤ ከሞቱት ሰዎች በተጨማሪ ሌሎች 15 ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል ተወስደዋል። በእሳት ቃጠሎው ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል አብዛኞቹ በሕንጻው ውስጥ የሚኖሩ ከውጭ ሀገራት የመጡ ሠራተኞች ናቸው።

የኩዌት የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ እሳቱ በቁጥጥር ስር ውሎ በሕንጻው ውስጥ ያሉ ሰዎችን ሕይወት የማዳን ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

ሜጀር ጄኔራል ኢድ አል-ኦዌይሃን ለሀገሪቱ ቴሌቪዥን እንደተናገሩት፣ የእሳት አደጋው የደረሰው ዛሬ ረቡዕ ማለዳ 12 ሰዓት ላይ ነው።

የኩዌት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ ፋሃድ ዩሱፍ አል-ሳባህ የአደጋውን ስፍራ በጎበኙበት ጊዜ የሕንጻው ባለቤቶችን የደኅንነት መመሪያዎችን በመጣስ እና "በገንዘብ ወዳድነት" መክሰሳቸውን የሮይተርስ ዜና ወኪል ዘግቧል።

የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት አደጋው የደረሰበት ሕንጻ ከሚገባው በላይ በርካታ ሰዎች ተጨናንቀው የሚኖሩበት ነው።

አንድ ከፍተኛ የፖሊስ መኮንን ለሀገሪቱ ቴሌቪዥን በሰጡት ቃል፤ አደጋው በደረሰበት ጊዜ "ከፍተኛ ቁጥር" ያላቸው ሰዎች በሕንጻው ውስጥ በተጨናነቀ ሁኔታ ይኖሩ ነበሩ።

"የበርካቶችን ሕይወት ለማዳን ተችሏል፣ ነገር ግን በጭስ በመታፈን ምክንያት የሞቱ ሰዎች አሉ" በማለት በእንደዚህ ዓይነት ለተጨናነቁ የመኖሪያ ሕንጻዎች ተደጋጋሚ የአደጋ ማስጠንቀቂያዎች ሲሰጡ መቆየታቸውን ገልጸዋል።

አደጋው በደረሰበት ሕንጻ ውስጥ የነበሩት የውጭ ሀገር ሠራተኞችን ዜግነት እና የቅጥር ሁኔታቸውን በተመለከተ እስካሁን ምንም ዓይነት ዝርዝር መረጃ አልወጣም።

ነገር ግን ያልተረጋገጡ ዘገባዎች በአደጋው ከሞቱት የተወሰኑት የሕንድ ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች መሆናቸውን ያመለክታሉ።

ከኩዌት ሕዝብ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት የውጭ ሀገር ሠራተኞች ሲሆኑ፤ ሀገሪቱ በተለይ በግንባታ ዘርፍ እና በቤት ውስጥ ሥራ ከውጭ ሀገራት በሚመጡ ሠራተኞች ላይ ጥገኛ ናት።

የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች በተደጋጋሚ በሀገሪቱ ያሉ የውጭ ሀገር ሠራተኞች የአኗኗር ሁኔታን በተመለከተ ስጋታቸውን ሲገልጹ ቆይተዋል።

## የሱዳኗ ወሳኝ ከተማ ኤል ፋሸር በአማጽያን እጅ ልትገባ እንደምትችል አሜሪካ አስጠነቀቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በምዕራባዊ ዳርፉር ትልቁ የሆነው እና በሱዳን ጦር ቁጥጥር ስር የሚትገኘው ብቸኛ ከተማ ኤል ፋሸር በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአማጽያኑ ቁጥጥር ስር ሊትወድቅ እንደምትችል በሱዳን የአሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ አስጠነቀቁ።

የሱዳን ጦር እና የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ከገቡ 14 ወራት ያስቆጠሩ ሲሆን፣ ከተማዋ በአማጽያኑ ከበባ ስር ትገኛለች።

በሱዳን የአሜሪካው ልዩ መልዕክተኛ ቶም ፔሪሎ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ የኤል ፋሸር ከተማን የሚቆጣጠሩ ከሆነ ዳርፉርን ከማዕከላዊ አስተዳደር ለመነጠል ይረዳናል ብለው ያምናሉ ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።


መልዕክተኛው "በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ" ሀገራቸው አሜሪካ ለዳርፉር የሀገርነት እውቅና እንደማትሰጥ ገልጸዋል።

ዲፕሎማቱ በፈጥኖ ደራሽ ኃይል ውስጥ ኤል ፈሸርን መቆጣጠር ዳርፉርን እንደ ሀገር መመሥረት አድርገው የሚያስቡ አሉ ካሉ በኋላ ከዚህ "የህልም ዓለም" ሊነቁ ይገባል ሲሉ አክለዋል።

ጨምረውም ካለፈው ሚያዝያ ጀምሮ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ጥቃቱን ባጠናከረባት ኤል ፋሸር ከተማ የተኩስ አቁም እንዲደረግም ጠይቀዋል።

"በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ከበባ ሚሊዮን ንጹሃን ሲራቡ እየተመለከትን ነው። የሚፈጸሙ የቦምብ ድብደባዎች ሆስፒታል ውስጥ ሰው እየገደሉ ነው። 45 ሺህ ነፍሰጡር ሴቶች በቂ ህክምና ብቻ ሳይሆን ለጤናማ እርግዝና የሚያስፈልግ ዕለታዊ ምግብ ለማግኘት ሲቸገሩ እየተመለከትን ነው። ኤል ፋሸር በቁጥጥር ስር የምትገባ ከሆነ ደግሞ ነገሮች እጅግ ይከፋሉ። አሰቃቂ ነገሮች ከጦርነት ሜዳ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ቦታዎችም እየሰማን ነው፤ ሰዎች ይሰደዳሉ" ብለዋል።

ይህ የአሜሪካ ማሳሰቢያ የመጣው ኤል ፋሸር ከተማን ለመቆጣጠር ደም አፋሳሽ ውጊያ ለሳምንታት ከተደረገ በኋላ ነው።



በአሁኑ ወቅት በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሲቪል ሰዎች መውጪያ ያጡ ሲሆን፤ በርካቶች ርሃብ እንዳንዣበበባቸው ተገልጿል። ይህም በተከሰተው የምግብ እና የውሃ እጥረት የመጣ ነው።

ኤል ፋሸር በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የሸሹ ሰዎች መጠለያ ነበረች። አሁን ግን ወደ ጦርነት አውድማነት እየተቀየረች ነው።

ሲቪል ሰዎች የውጊያ ሰለባ እየሆኑ ሲሆን፤ ሆስፒታል እና መሰል ተቋማትም የጥቃት ኢላማ እንደሆኑ እየተዘገበ ነው።

በከተማው አንድ የጤና ማዕከል ብቻ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በሆስፒታሉ አንድ የቀዶ ህክምና ባለሙያ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፤ እሱም ያለ እረፍት ለመሥራት ተገዷል።

በኤል ፋሸር የሚደረገው ተደጋጋሚ ውጊያ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ እያደረገ ነው። በርካቶች ደኅንነቱ የተጠበቀ ስፍራ በመፈለግ ወደ ሱዳን ምዕራባዊ ክፍል እየተመሙ ይገኛሉ።

የአሜሪካው ዲፕሎማት ፔርሎ "ይህንን ማቆም አለብን። ይህንን ጦርነት ለማቆም መረጋጋት ይኖርብናል" ብለዋል።

ባለፈው ዓመት ሚያዝያ ላይ የተቀሰቀሰው የሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት በተቀናቃኞቹ የሀገሪቱ ጦር አዛዥ ጄኔራል አል ቡረሐን እና ጄኔራል ሐምዳን ዳጋሎ በሚመሩ ኃይሎች መካከል እየተካሄደ ይገኛል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።



የ250 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ይፋ ሆኗል፤

# በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች 2 ሺህ የጤና ማዕከላት ሊገነቡ ነው

## - አራት ሚሊዮን ዜጎችን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ያደርጋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በተመረጡ ገጠራማ አካባቢዎች ሁለት ሺህ የጤና ማዕከላት መገንባት የሚያስችል የ250 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ይፋ ሆኗል። ፕሮጀክቱ አራት ሚሊዮን ዜጎች የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተጠቁሟል።

አራት ሚሊዮን ዜጎችን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርገውን የአራትዮሽ ስምምነት የጤና ሚኒስቴር ፣ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ቦንጋ ዩኒቨርሲቲና በሩሲያ የፓን አፍሪካ ፐብሊክ ፕራይቬት ትብብር ልማት ማዕከል ትናንት ተፈራርመዋል።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጄ ድጉማ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ በአምስት ዓመት የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ በተመረጡ የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች ሁለት ሺህ የጤና ማዕከላት ይገነባሉ።

አጠቃላይ እንደ ሀገር በአማካኝ አራት ሚሊዮን ዜጎች የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመው፤ የሚገነቡት የጤና ማዕከላት ከነባር ጤና ኬላዎች ጋር ተጣጥመው የሚሰራባቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንደገለጹት፤ በጤና ማዕከላቱ የወሊድ አገልግሎት፤ የቅድመ እርግዝና እንክብካቤ፣ የቤተሰብ እቅድ፣ የክትባት አገልግሎትና የሕፃናት ሕክምና አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

ለአረጋውያንና እድሜያቸው ለገፉ ሰዎች ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ጋር ተያይዞ ሕክምናና እንክብካቤ ይሰጣል ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ ማዕከላቱ በጤና ኬላዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ማዕከላቱ የማህበረሰብን የጤና ግንዛቤና የጤና ተቋም አገልግሎት ተጠቃሚነት ከፍ እንደሚያደርጉ አንስተው፤ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት እንደሚያስችሉ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያና ሩሲያ በጤናው ዘርፍ በጋራ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ እንደሚገኝ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተደረገው ስምምነት የጤና ዘርፉን በተለየ መልክ ለማሳደግ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል።

በሩሲያ የፓን አፍሪካ ፐብሊክ ፣ፕራይቬት ትብብር ልማት ማዕከል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ አክሳና ማዮሮቫ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ ለእናቶችና ሕፃናት እንዲሁም ለአረጋውያን የተሻለ የጤና አገልግሎት ለማቅረብ ያስችላል።

ኢትዮጵያ እና ሩሲያ የረጅም ዓመት ታሪክ ያላቸው መሆኑን አስታውሰው፤ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጠንካራ ግንኙነት እንዳላቸው አውስተዋል። የአሁኑ ስምምነት የሀገራቱን ግንኙነት በማሳደግ ረገድ አዎንታዊ ሚና እንደሚጫወት ተጠቁሟል።

ፕሮጀክቱ የተጀመረው በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አነሳሽነት ሲሆን፤ በመጀመሪያ ዓመት 50 የጤና ማዕከላት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እንደሚገነቡ ተገልጿል። በቀጣዮቹ ተከታታይ ዓመታት ቀሪዎቹ የጤና ማዕከላት በሀገሪቱ በተለያዩ የገጠር አካባቢዎች እንደሚገነቡ ተገልጿል።

# የኦሮሚያ ክልል ከ413 ሚሊዮን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይገኛል።በክልሉ በክረምት ወቅት ከ413 ሚሊዮን በላይ የሻይ ቅጠል ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት ተደርጓል።

በተለይ የሻይ ቅጠልን እንደ አቮካዶና ሌሎች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በስፋት አልምቶ ለሀገር ኢኮኖሚ ለማዋል በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤የሻይ ቅጠል ልማት ከተጀመረብት 2013 ዓ.ም ጀምሮ አንደ ሀገር ሁለት ሺህ ሄክታር ብቻ እየለማ ከነበረበት አሁን ላይ አርሶ አደሩን ከኢንቨስተሩ ጋር በማስተሳሰር አቅምን የመሳደግ ሥራ በስፋት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ መሐመድሳኒ ገለጻ፤ እንደ ሀገር የሻይ ቅጠልን አልምቶ ለገበያ ለማቅረብ ሰፊ አቅም ያለ ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት ሻይ ቅጠል ከውጭ ሲገባ ነበር። በክልልም ሆነ በሀገር ደረጃ ችግሩን ለመቅረፍ ተብሎ የሻይ ቅጠል ልማት ላይ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው።

የሻይ ቅጠል ልማት እስከ 2015ዓ.ም ከኢንቨስትመንት ወጪ በአርሶ አደር ማሳ ላይ ተጨማሪ 522 ሄክታር ማልማት መቻሉን ጠቅሰው፤ ይህንኑ በማስፋት በ2016 ዓ.ም እቅድ ተይዞ በ30ሺህ ሄክታር ላይ የሻይ ቅጠል ለማልማት ከ413 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በማፍላት ለተከላ ለማድረስ እንክብካቤ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

የችግኝ ተከላው የሚከናወነው በክላስተር ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት የችግኝ ዝግጅት አልቆ የመሬት መረጣ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

በአግባቡ ማልማት በሚችልበት ሁኔታ ለአርሶ አደሩና ለአመራሩ ግንዛቤ ተሰጥቶ ተከላ ሊጀመር መሆኑንም ነው የጠቀሱት።

የሻይ ቅጠል ልማት ከተከላው ባሻገር እንክብካቤ ይፈልጋል ያሉት አቶ መሐመድሳኒ፤ አቀነባብሮ ወደ ሻይነት ለመቀየር ፋብሪካ እንደሚፈልግ ጠቅሰዋል።

የክልሉ መንግሥት ከተለያዩ አካላት ጋር በመነጋገር እያንዳንዱ ክላስተር ላይ ፋብሪካ እንዲቋቋም እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

“የዛሬ 10 ዓመት ሻይ ቅጠል ከውጭ ወደ ሀገር ቤት ይገባ ነበር። ኢንቨስተሮች በሰፊው ማልማት በመጀመራቸው በአሁኑ ወቅት የሻይ ቅጠል ፍጆታ በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን ተችሏል። ጎን ለጎንም ወደ ውጭ እየተላከ ነው። በዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በዓመት በአማካይ ሁለት ሚሊዮን ዶላር እየተገኘ ሲሆን፤ 70 በመቶ ያህሉን የሚሸፍነው ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ነው” ብለዋል።

የውጭ ምንዛሬን በስፋት ለማግኘት፣ የልማት ሥራውን በስፋት ለማሳደግና ተሞክሮን ለሌሎች ክልሎች የማስፋት ሥራዎች እየተሠሩ እንዳለም አቶ መሐመድሳኒ ገልጸዋል።

# ተረጂዎችን በተመለከተ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማናር በስፋት ይስተዋላል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ይህ የሚደረገው የተረጂውን ቁጥር በመቶዎች እጥፍ በማሳደግ የተለየ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ነው። የራስ ወገን ተቸግሮ እንዲህ አይነት ሥራ መሥራት በችግር ውስጥ ባሉት ወገኖች ላይ ሞት እንደ መፍረድ ያህል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞንና በከተማ ደረጃ ተረጂዎችን ለመደገፍ የሚያስችል በቂ አቅም መኖሩን ገልጸው፤ ከዚህ ያለፈ ሆኖ ሲገኝና ቅጽበታዊ አደጋዎች ሲከሰቱ ደግሞ ኮሚሽኑ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል እህል በሰላሳ ቢሊዮን ብር ተገዝቶ ለተረጂዎች መሰራጨቱን ነው የተናገሩት።

ኮሚሽኑ ኅብረተሰቡ ድረስ በመሄድ ድጋፍ የማከፋፈል ሥራ እንደማያከናውን አመልክተው፤ድጋፉ ከኅብረተሰቡ ጋር በትክክል መድረሱ የቀበሌ ፣ የወረዳና የዞን አመራሮች ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።

ለተረጂዎች የሄደውን ድጋፍ በተገቢው መልኩ ተደራሽ ያላደረጉ አካላትን እስካሁንም ባለው የሕግ አግባብ በመጠቀም ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረጉን አመልክተው፤ በዚህም 500 የሚደርሱ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ወቅት የተወሰኑት በእስር ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ከኃላፊነትና ከሥራ የታገዱ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች እንዲሸጋሸጉ የተደረጉ መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

በዘላቂነት ችግሩን ለመፍታትም ተጠያቂነትን የሚያስከትል አዲስ የተዘጋጀው ፖሊሲ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

# መንግሥት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተግባራዊ በማድረግ ብዙ ርቀት መጓዙን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ፓርቲ አባል ኮማንደር ገብረመስቀል ገብረሚካኤል ገለጹ።

የትዴፓ ፓርቲ አባል ኮማንደር ገብረመስቀል ገብረሚካኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤መንግሥት የፕሪቶሪያው ሰላም ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ርቀት ተጉዟል። በትግራይ ክልል የሰብዓዊ አቅርቦት ተደራሽ በማድረግ፣ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ በመገንባት፣ በጀት በመመደብ፣ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግና ሌሎች ሥራዎችን በማከናወን የፕሪቶሪያው ሰላም ስምምነት ተፈጻሚ እንዲሆን ብዙ ረቀት ተጉዟል።

በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረገውን የፕሪቶሪያው ሰላም ስምምነት ተከትሎ መንግሥት ብዙ አወንታዊ ሥራዎች በክልሉ ሠርቷል ያሉት ኮማንደር ገብረመስቀል፤አሁንም መንግሥት ኃላፊነቱን በሚገባ እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ ኮማንደሩ አገላለጽ፤የፌዴራል መንግሥት በተለይ ከስምምነቱ ማግስት ጀምሮ ከሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ጋር ተያይዞ እየሠራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ ፣ቴሌኮም እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶች እንዲሟሉ አድርጓል። የጤና ተቋማት ተመልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉም የሚመሰገን ነው።

ሥራቸውን አቁመው የነበሩ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።በዚህም የተነሳ ብዙ ፋብሪካዎች ወደ መደበኛ ሥራቸው መመለሳቸውን አውስተው፤መንግሥት የሰላም አስፈላጊነትን በማመኑ ብዙ ወጪ በማውጣት በርካታ መሠረተ ልማቶችን ወደ ቀድሞ ሥራቸው እንዲመለሱ አድርጓል።በጥቅሉም በርካታ አወንታዊ ሥራዎችም ሠርቷል ነው ያሉት ።

መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ እያቀረበ መሆኑን ገልጸው፤ይሁን እንጂ እርዳታ ከሚያስፈልገው የሰው ቁጥር ጋር ሲነፃፀር ውስንነት ቢኖርም ሕዝቡ እርስ በርስ መደጋገፍ ክፍተቱን መሸፈን እንደሚኖርበት ጠቁመዋል።

የሰላም ስምምነቱ ካስቀመጠው ግዴታ ባለፈ የፌዴራል መንግሥት መተማመን ለመፍጠር እና ሰላም ለማጠናከር ያስፈልጋሉ ያላቸውን ፖለቲካዊ እርምጃዎች በተከታታይ መውሰዱን ጠቅሰው፤ ሰብአዊ ድጋፍም ያለ ምንም እንቅፋት ወደ ክልሉ የሚደርስበት ሁኔታ መፍጠሩን አስገንዝበዋል።

እንደ ኮማንደር ገብረመስቀል በክልሉ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማት ሥራ እንዲጀምሩ አስችሏል።የስምምቱ አተገባበር የተወሰነ ክፍተት ቢኖርበትም በፌዴራል መንግሥት በኩል ስምምነቱን ለመፈጸም የተደረጉ ሥራዎች የሚደነቁ ናቸው።

የሰላም ስምምነቱ ከትግራይ ሕዝብ ባሻገር ለኢትዮጵያ ሕዝብም ተጨባጭ ጥቅም ማስገኘቱን አመልክተው፤በስምምነቱ መሠረት ዘላቂ ሰላም እንዲፀና የፌዴራል መንግሥት እና ሕወሓት በቆራጥነት ሊሠሩ እንደሚገባም አመልክተዋል።

ታጣቂዎች ሙሉ በሙሉ ትጥቅ አለማስፈታቸውና ተፈናቃዮች ወደ ነበሩበት አለመመለሳቸው የስምምነቱ ክፍተቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት የሰው ልጆች ህይወት መቀጠፍንና የንብረት ውድመትን የታደገ ነው ያሉት ኮማንደሩ፤በስቃይ ውስጥ ለነበረው ሕዝብ የትግራይ ሕዝብ ትልቅ እፎይታ የሰጠ መሆኑን ተናግረዋል ።

እንደ ኮማንደሩ አገላለጽ፤ስምምነቱ ለኢትዮጵያም ይሁን ለአፍሪካ ብዙ ትምህርት ያስገኘ ነው። ምክንያቱም በቀላሉ መተማመንን መፍጠር ከባድ ነው።በተለይ ፖለቲካዊ ችግርን በንግግር የመፍታት ባህል እንዲዳብር በር ከፋች ነው፤ይህ ለሌሎች ታጣቂ ኃይሎችም ትምህርት ሊወስዱበት የሚገባ ነው።

የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም መደረጉ የሚታወስ ነው።

# ስፖርት





## አካዳሚው በተለያዩ ርቀቶች የተሰጥኦ ልዩታ ማዕቀፍ ይፋ አደረገ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ የ5ሺ ሜትርና የ3ሺ ሜትር መሠናክል የተሰጥኦ (ታለንት) ልየታ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ይፋ አደረገ። አካዳሚው 9ኛውን ሃገር አቀፍ የስፖርት ሳይንስ ጥናትና ምርምር ጉባኤውን በቢሾፍቱ ከተማ ትናንት አካሂዷል፡፡

ታዳጊ ስፖርተኞችን በመመልመል በሳይንሳዊ ስልጠና ለክለቦችና ብሄራዊ ቡድኖች የሚያበቃው የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ፤ ውጤታማነቱን በውድድሮች ላይ በሚያሳትፋቸው ስፖርተኞቹ አረጋግጧል። ከእነዚህ ስፖርቶች መካከል አትሌቲክስ ተጠቃሽ ሲሆን በ5ሺ ሜትር እና 3ሺ ሜትር መሰናክል ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስኬታማ አትሌቶችን አፍርቷል። ይህንንም ተከትሎ በዘርፉ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለውጤታማነት የሚያበቃ ማዕቀፍ በማዘጋጀት አስመርቋል።

ማዕቀፉ የምልመላ ስታንዳርድ፣ የአሰለጣጠን ዘይቤ፣ ምዘና እና ልኬትን አካቷል። አካዳሚው ውጤታማ የሆነበት ይህ ሞዴል በተግባር የተፈተሸ በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስፖርቱን ሊጠቅም እንደሚችልም ታምኖበታል። በቀጣይም በእግር ኳስ እና ሌሎች ስፖርቶች የሚዘጋጅ ይሆናል።

ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች መካከል የስፖርት ጥናትና ምርምር ማካሄድ አንዱ የሆነው አካዳሚው ዓመታዊ ጉባኤው ላይም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር አመራሮች፣ ክልሎች፣ የስፖርት ማህበራትና ተቋማት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተወጣጡ የስፖርት ሳይንስ ምሁራን እንዲሁም የስፖርት ሙያተኞች ተካፍለዋል፡፡ "ከቤተሙከራ ወደ መስክ፥ ስፖርትን በምርምር መቀየር" በሚል መሪ ቃል በተካሄደው ጉባኤ የተለያዩ ጥናታዊ ስራዎች ቀርበዋል።

በአካዳሚው የጥናትና ምርምር ማማከር ምክትል ዳይሬክተር አመንሲሳ ከበደ (ዶ/ር)፤ አካዳሚው በዘርፉ




**አካዳሚው በአትሌቲክስ ስፖርት የምልመላና ምዘና ሞዴል ሲያዘጋጅ በቀጣይም በእግር ኳስና ቅርጫት ኳስ ስፖርቶች ላይ መሰል ስራዎችን ያከናውናል፤**

የአደረጃጀት ማሻሻያ በማድረግ በጥናትና ምርምር ዘርፍ ግምባር ቀደም ለመሆን እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። ጥናቶቹ ከአካዳሚው ሙያተኞች ባለፈ ከሀገርና የውጪ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን እየተከናወነ ሲሆን፤ ትኩረቱንም በስፖርት ችግር ፈቺ ጥናቶችና አሰራሮች ላይ አድርጓል። በአትሌቲክስ ስፖርት የምልመላና ምዘና ሞዴል ሲያዘጋጅ በቀጣይም በእግር ኳስና ቅርጫት ኳስ ስፖርቶች ላይ መሰል ስራዎችን የሚያከናውን ይሆናል። ከስፖርት ተቋማት ጋር በመሆንም መሰል ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

አካዳሚው ከምስረታው አንስቶ ባለፉት 13 ዓመታት 207 የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሰራጨቱን የሚገልጹት የአካዳሚው ዳይሬክተር አቶ አምበሳው እንየው፣ አካዳሚው ከራሱ አቅም ባለፈ ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን የተሰሩት እነዚህ ጥናቶች መድረክ እንዲያገኙ፣ እንዲሰራጩና ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል ብለዋል። ከዚህ ባለፈ ቤተሙከራዎችን በማደራጀትና በማበልጸግ የታዳጊ ሰልጣኞችንና ሌሎች ቡድኖችን ልኬቶችንና ግምገማ በማከናወን ላይ መሆኑንም አብራርተዋል።

በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፤ የጥናትና ምርምር ስራዎች በየትኛውም ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን ጠቁመዋል። በስፖርቱ የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተግባራዊ በማድረግና የፖሊሲ አካል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም አብራርተዋል። የአካዳሚው ዓላማ ከግብ እንዲደርስም ሳይንሳዊ ጥናቶችን አጠናክረው መቀጠልና ዘመናዊው ስፖርት በሚፈልገው ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል። ለዚህም ባለድርሻ አካላት ተሳትፏቸውን ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊ ወጣቶች በመመልመልና በማሰልጠን ለሃገርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት፣ የስፖርት ባለሙያተኞችን አቅም ለመገንባት እንዲሁም በስፖርቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን የሚፈታና ለስፖርት እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል ጥናትና ምርምር ማካሄድ ናቸው፡፡ ከአካዳሚው ባለሙያዎች ባለፈ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለሙያዎች የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በማሰራጨት የሃገሪቱ ስፖርት ልህቀት ማዕከል የመሆን ዓላማንም አንግቧል፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካትም አካዳሚው ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የስፖርት ጥናትና ምርምር ጉባኤውንም በየዓመቱ በማካሄድ ችግር ፈቺ የጥናት ውጤቶች መድረክ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ጥናቶቹ መድረክ ከማግኘት ባለፈ እንዲታተሙ በማድረግ የስፖርት ማህበራት፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲሁም የስፖርት ተቋማት ተደራሽ ሆነው ተግባር ላይ እንዲውሉም ይደረጋል፡፡ ካለፈው ዓመት ጀምሮም ይፋ በሆነው ድረገጽ አማካኝነት ጥናቶቹን በመለጠፍ የዘርፉ ባለሙያዎች በቀላሉ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው፡፡

## ድጋሚ የሐራጅ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት አባያ ገላና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ እና በፍ/ባለዕዳ እነ ሞራል ኢኪፕመንት ሬንታል ኃ/የተ/የግ/ማ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 162452 በ24/12/2012 ዓ.ምእናመ/ቁ 284462 በ26/8/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቂርቆስ/ክ/ከተማ ወረዳ 9 ደንበል ህንፃ ግቢ ውስጥ ቆሞ የሚገኘውን የተለያዩ የእርሻ መሣሪያ ማሽኖች መሳተፍ የሚፈልግ ተጫራች በፌ/ፍ/ፍ/አፈ/ዳይሬክቶሬት በሚል C.P.O 4ኛ 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር ) በማሲያዝ ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ አሁን የሚሸጠው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428/1 መሰረት ነው፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.PO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ C.P.O የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም C.P.O አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር 1000191874564 አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በፌዴራል የፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

## የሐራጅ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ እና በፍ/ባለዕዳ መርዕድ ታደሰ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 252549 በ10/12/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 300704 በ24/8/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ የድርጅቱ መኪና ማቆሚያ ግቢ ውስጥ ቆሞ የሚገኘው የሠ.ቁ ኮድ 3-53006 አ.አ የሆነው ሀይሉክስ ድርብ ተግባር መኪና የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 2,000,000(ሁለት ሚሊዮን ብር ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆነ ታውቆ ሐምሌ 10 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆኑ አሳንሶ C.P.O የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም C. P.O አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በፌዴራል የፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**